# የተጠላው ንጉሥ

... የጌታ ክብር ዛሬ በቃሉ አገልግሎት አማካኝነት በእኛ ላይ ይመጣል። እና በ...

2 ባለፈው ሳምንት፡ እኔ ትንሽ የአየር ሁኔታዬ ጥሩ አልነበረም። በትክክል የአየር ሁኔታ ማለቴ አይደለም፡ መመርመር ነብረብኝ፡ አካላዊ ምርመራ ማድረግ ነበረብኝ። ሆስፒታል እንደነበርኩም፡ ሰምታችኋል። ወደዚያ የሄድኩትም ወንዙን ተሻግሬ መመላለስ እንዳይሆንብኝ አሰቤ ነው። የላይኛው የአመጋገብ ሁኔታ እና፡ የታችኛውን የምግብ ሁኔታ ያያሉ። በየጥቂት ደቂቃውም፡ ተመልሰው በመምጣት፡ እንደገና ኤክስ-ሬ ያያሉ። ነገር ግን የውጭ አገር ተልዕኮዎችን ማከናወን ሲኖርብን፡ በየስድስት ወሩ፡ መጠጣት አለብን። ወንድም ሮበርትስ እና ጓደኞቹ፡ ይመስለኛል፡ በየስድስት ወሩ ይጠጣሉ። እኔ ግን ለአራት ዓመታት አንድም ቀን ወስጄ አላውቅም።

3 ችግሩ፡ ያንን ካስተር ኦይል አልወደውም፡ ያ ብቻ ነው። እና በምትኩ መስጠት የሚችሉት ሌላ ምንም ነገር እንደሌለ ይናገራሉ፡ ስለዚህ እኔ፡ ኦ፡ ያንን ነገር ሲሰጡኝ በጣም እታመማለሁ። ታውቃላችሁ፡ በሕይወቴ ታሪክ ውስጥ፡ ያ ነገር እንዴት፡ እንደሚያሳምመኝ ነግሬያችኋለሁ። እ—እናም ብቻ ያንን ነገር መውሰድ እጠላለው። እናም ዶክተሩ ጓደኛዬን እንዲህ አ... አልኩት፡ "ሌላ ነገር የለም? "

እርሱም፡ "አይመስለኝም፡ ወንድም ብራንሀም" አለኝ።

4 ኦህ፡ ሴቲቱ ይዛው ስትመጣ፡ የመሰለኝ፡ ምናልባት እያጋነንኩት ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን፡ አንድ ሊትር ያክል ይመስላል። እ—እሱ... እንዲህ ብዙ አይቼ አላውቅም። ብቻ አፍንጫዬን ይዤ አፌንም በማፊኛ ይዤ ነበር። ነገር ግን በመጨረሻ እንዴትም ወርዷል።

5 ነገር ግን አሁን፡ በሙከራ ሁሉ ውስጥ፡ እና ሁሉም ነገር አልፏል፡ ለነበረኝ ጥሩ ምርመራ ጌታን ማመስገን እፈልጋለሁ። ምርመራውን መቶ በመቶ፡ አልፌያለሁ፡ በዓለም ላይ ወደፈለግኩት ቦታ መሄድ እችላለሁ። ሉዊስቪል ውስጥ፡ ሦስት ምርጥ ብ—ብዬ፡ ማሰባቸውን፡ ስፔሻሊስት ዶክተሮችን፡ ጠየኳቸው። እናም ጠየኳቸው፡ "ቢያንስ አሥር በመቶ የአካል ጉዳተኛ ነኝን? " አልኳቸው።

6 "ምንም ዓይነት የአካል ጉዳት የለብህም፡" አሉኝ። "በሁሉም፡ ፍጹም ጤንነት ላይ ነህ፡" እ—አሉኝ። እግዚአብሔርን በጣም አመሰግነዋለሁ። እንደዛ መሆን፡ ከሰማያዊ አባታችን በስተቀር ከሌላ ከማን ሊመጣ ይችላል፡ አያችሁ?

7 እርሱም እንዲህ አለኝ፡ "የአንተ... ዝውውሮችህ በሙሉ፡ የሚያሳየው፡ ወጣት እንደሆንክ ነው።" "የደምህ ህዋሶችህ እንኳን፡ መሰበር ሆነ ሌላ ነገር አልጀመሩም፡" አለኝ። "በጣም ጥሩ ቅርጽ ላይ ነህ፡ ወንድም ብራንሃም፡" አለኝ።

እኔም "እሺ፡ በጣም ደስ ብሎኛል፡" አልኩት።

8 በዛ ሆስፒታል ውስጥ ላሉት፡ ለሁሉም ነርሶችና፡ ለሁሉም ዶክተሮች፡ ስለ አምላክ መንግሥት የመመሥከር እድል አግኝቼ ነበር። እና አንድ ሐኪም፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ይገኛል ብዬ አስባለው። እናም... በ—በዚህ ዓለም ውስጥ አሁንም ጥሩ ሰዎች እንዳሉ በማወቄ ደስ ብሎኛል፡ ለአምስት ቀናት የሰውነት ምርመራ ያደረጉሉኝ ሰዎች፡ እውነተኛ ሰዎች፡ ምናልባትም ለእያንዳንዳቸው ሁለት ወይም ሦስት መቶ ዶላር ሊያስከፍለኝ ይችል ነበር። ታክሜ ስጨርስ፡ “ይህ ለምትሰራው የጌታ ሥራ የምናደርገው፡ አስተዋጽኦ ነው፡” አሉኝ። አያችሁ? አዎን። ሌላው ቀርቶ... እንዲህ አሉኝ፡ “ለምን፡ ልትከፍለን አሰብክ፡ አሳፍርከን።” “ብቻ ጸልይልን!” አሉኝ፡

9 “በውስጣችንም፡” “እኛ ልንረዳው የማንችለው የሆነ ስሜት አለን፡” አሉኝ። እኔም እንዲህ አልኩ... “እ... እ—እንደዚያ አይመስልም... ” እሱም እንዲህ አለ፡ “ውጫዊ አካልህ፡ ጭንቀትም መረበሽም አይታይብህም። ነገር ግን፡” “በውስጥህ፡ ልንረዳው የማንችለው የሆነ ስሜት አለ፡” አለኝ።

10 “ለአፍታ ቁጭ ብለህ ብትጠይቀኝ፡ እነግርሃለሁ፡” አልኩት። እኔም ስለ ራዕዮቹ ማውራት ጀመርኩ። ለእነሱ አዲስ ነገር ነበር። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ነግሬያቸዋለሁ። ምንም ነገር አያውቁም ነበር። ከዚያም ጌታ በቀደም ያሳየኝ ራዕይ ነገርኳቸው፡ እነርሱም እንደ ሕፃናት አለቀሱ። እዚያ ቁጭ ብለው አለቀሱ። እና እኔ... እነሱ... እንዲህ አልኳቸው፡ “እኔን እንደ አንድ የሃይማኖት እብድ ወይም እንደ ሌላ ነገር እንደማታስቡኝ ተስፋ አደርጋለሁ።”

11 እንደኛው “ወንድም ብራንሃም፡ በፍጹም። በሙሉ ልቤ አምናለሁ፡” አለኝ። “ነገር ግን አንድ ነገር ብቻ መናገር እፈልጋለሁ፡ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ለመማር ወደ ትምህርት ቤት አትሄድም፡” አለኝ። “ሁሉን ቻይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጡ አምናለሁ፡” አልኩት። እነሱም አሉ የተባሉ፡ በሉዊቪል ከሚገኙት ምርጥ ሐኪሞች መካከል ሦስቱ ነበሩ። ለዚህም፡ በጣም ደስተኛ ነበርኩ፡ ምናልባትም፡ ጌታ እዚያ የተወሰነ ዘር እንድዘራ እንደፈለገ አውቄ ነበር።

12 ለእያንዳንዱ ነርስ፡ ተናገርኩ። እነርሱ፡ አንድ ቀን፡ ጠዋት፡ ከኤክስ-ሬ ክፍል ሰወጣ አንዳቸውን... አንዲት ምስኪን አሮጊት አየሁ። በጣም ታማለች። እስከምደርስባት ድረስ፡ ወደ ታች መውረዴን ቀጠልኩ። እየሞተች ያለች መሰሎኝ ነበር። እኔም “እህቴ፡ አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ፡” አልኳት።

እሷም “ጠይቀኝ፡ ወዳጄ፡” አለችኝ።

“ክርስቲያን ነሽ? ” አልኳት፡

እሷም “**የሆነ** ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ፡” አለችኝ።

13 እኔም “ትንሽ ግልጽ ላድርግልሽ፡” አልኳት። እንዲህ አልኳት፡ “እ—እውነተኛ ክርስቲያን መሆንሽን፡ ማወቅ እፈልጋለሁ። ማለቴ፡ ይህን የሕይወት ባሕር አልፈሽ፡ ወደ ሌላኛው ምድር መሄድሽ፡ ትወጅዋለሽን? ” “በእርግጥ ትድኛለሽን? ” አልኳት፡

እሷም “አዎ፡ ጌታዬ። እድናለሁ፡” አለችኝ።

14 እኔም፡ “እግዚአብሔር ልብሽን ይባርክ። እንደዚያ ካመንሽ፡ ነፋሱ በየትኛውም አቅጣጫ ቢነፍስ፡ ችግር የለብሽም” አልኳት።

15 እኛ ዞር ብለን ከመረመርን፡ አሁንም በዓለም ላይ ብዙ ጥሩ ሰዎች አሉ።

16 አሁን፡ ዛሬ፡ በኋላ ላይ የምነግራችሁ አንድ ራእይ ይዤ መጥቻለሁ። በመጀመሪያም፡ ከቃሉ የተወሰነ ክፍል መናገር እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም ቃሉ በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ፡ አሁን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። እና ቻርሊ ኮክሰን፡ እና፡ ወንድሜ፡ ጓደኛዬ፡ እዚያ አብረው ቆሞ በማየቴ ደስ ብሎኛል። ወንድም፡ ማስታወስ አልቻልኩም... ጄፍሪስ፡ ስሙን ማስታወስ አልቻልኩም። ከጆርጂያና፡ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተውጣጣችሁ ውድ ወንድሞቻችን። የጥንቱ ጓደኛዬ፡ ቢል፡ እዚህ ተቀምጦ ነበር፡ ዛሬ ጠዋት፡ እሱ እንደሆነ አምናለሁ። እና—እና ብዙ... እና አንድ ወንድም ከጆርጂያ ይታየኛል፡ ይህን ሙሉ ልብስ የሰጡኝ የጆርጂያ ሰዎች ናቸው። ታውቃላችሁ፡ ይህ—ይህ በሕይወቴ ከለበስኳቸው ምርጥ ልብሶች አንዱ ነው። በጣም ምቾት አለው፡ እውነት በጣም ቆንጆ ነው። እና ለእናንተ ትልቅ ቦታ አለኝ። ባለፉት ጥቂት ቀናት፡ ምን እንደደረሰብኝ ስነግራችሁ፡ ያ ለእኔ፡ ለምን ትልቅ ትርጉም እንዳለው ትረዳላችሁ።

17 አሁን፡ ጌታ ከፈቀደ፡ አንድ ነገር አምናለሁ፡ በሕይወቴ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ፡ ጠንከር ያለ ውጊያ ማድረግ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም፡ አሁን ሲገባኝ... በእርግጥ፡ ዛሬ ልሞት እችላለሁ። እንደዚያ ነው፡ አይታወቅም። የእኔ ኤሌክትሮ-ካርዲዮግራም እና ሌሎችም ምርመራዎች፡ አሥራ ሰድስት የተለያዩ የኤክስ-ሬይ ዓይነቶች፡ አዎ፡ የተሟላ አካላዊ ምርመራ፡ እኔ... እንደ ማንኛውም፡ በምድር ላይ እንዳለ ሰው ጤነኛ እንደሆንኩ አሳይቷል። ለዚህም አመሰግናለሁ። ነገር ግን፡ እነዚህ ሁሉም ነገሮች፡ እንዲያውም፡ ከዚህ ሁሉ ነገር በኋላ፡ እኔ፡ አሁንም በአገልግሎቱ እንደሚጠብቀኝ ስለማምን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡ ይህም እርሱ ከትንሽ ጊዜ በፊት ያሳየኝ ነገር አልነበረም፡ እያችሁ፡ ብቻ በጣም ደስተኛ አደረገኝ።

18 አሁን፡ ይመስለኛል፡ ዛሬ ማታ... ሁሉም ሰላም ነው? [ወንድም ኔቪል፡ "አዎ፡ ወዳጄ፡" አለ።—እርታዒ።] ውድ—ውድ ወንድማችን ራ—ራስ ወዳድ ያልሆነ ሰው ቢኖር፡ ወ—ወንድም ኔቪል ነው። እና ባለፈው እሁድ እዚህ የነበረና ያመጣውን አስደናቂ መልእክት የሰማ ካለ፡ ባለፈው እሁድ፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፡ እግዚአብሔር ወደሰበሰበው ወደዚህ ትንሽ መንጋ "የማሰሮ ዘይት፡" በሚል፡... ርዕስ፡ ወንድም ኔቪል፡ ያመጣው መልእክት፡ በህይወቴ ከሰማኋቸው ሁሉ በጣም አስደናቂ ነበር።

19 እንዲሁም ጌታን ካስደሰተው፡ ወንድም ኔቪልን፡ እና ቤተ ክርስቲያኑን የሚያስደስት ከሆነ፡ ዛሬ ማታ እንደገና አዲስ ተከታታይ ትምህርት መጀመር እፈልጋለሁ፡ ከዚያም፡ ሰኞ ምሽት... ማለቴ፡ እሁድ ምሽት፡ ረቡዕ ምሽት፡ እና በሚቀጥለው እሁድ፡ ያጠናሁትን ተከታታይ ትምህርት አስተምራችኋለሁ።

20 እዚያ ሆስፒታል ውስጥ መቈየት አልነበረብኝም ነበር። ነገር ግን እነሱ ለእኔ በጣም ጥሩ ነበሩ፡ ከክፍሉ ዋጋ አንድ-ሦስተኛ ብቻ ነበር ያስከፈሉኝ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱሶቼንና፡ መጽሐፎቼን ወሰጄ፡ አልጋውን አዘጋጅቼ፡ ሁሉንም እዚያው አዘጋጅቼ አስቀመጥኩና፡ እዚያው ቁጭ ብዬ መጽሐፍ ቅዱሶቼንና ሌሎች ነገሮችን ማንበብ ጀመርኩ። እናም ያንን የካተር ኦይል እስከያመጡልኝ ድረስ፡ በጣም ጥሩ ጊዜ ነበረኝ። መልካም ጊዜዬም በዚያው አበቃ። በ—በዚያን ጊዜ ጨረስኩ። ነገር ግን፡ ወንድም ፓት፡ በጣም አሞኝ ነበር። ያንን ነገር፡ በጭራሽ መቋቋም አልችልም። እና፡ ነገር ግን እስከ

የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወይም አራት ቀናት፡ ጥሩ ጊዜ ነበረኝ። ጥሩ ጊዜ እያሳለፍኩ ነበር።

21 የኤፌሶን መጽሐፍን እያጠናሁ ነበር። ኦህ፡ ያ ቤተክርስቲያን በህብረት ስትሆን! በጣም ቆንጆ ነገር እንደሆነ አስባለሁ።

22 እ—እናንተም፡ አሁን፡ የምትሄዱበት ቤተ ክርስቲያን ካላችሁ፡ በቀጥታ ሂዱ እና ግዳጃችሁ ላይ ተገኙ። ነገር ግን ቤተክርስቲያን ከሌላችሁ፡ እናም ዛሬ ማታ፡ ረቡዕ ምሽት፡ እና እሁድ ምሽት ተመልሳችሁ መምጣት ከፈለጋችሁ፡ ዛሬ ማታ፡ የኤፌሶን መልእክት 1ኛ ምዕራፍ፡ ረቡዕ ምሽት ደግሞ፡ የኤፌሶን መልእክት 2ኛ ምዕራፍን፡ ማስተማር እፈልጋለሁ፡ እና የፊታችን እሁድ ደግሞ፡ የኤፌሶን 3ኛ ምዕራፍ በመውሰድ፡ ቤተክርስቲያኗንቷን ለማስተካከል እፈልጋለሁ። ምን ማለቴ እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ወ—ወደ ቦታዋ፡ መመለስ ነው። ቤተክርስቲያንቷንም በደምብ-ይገነባታል፡ ብዬ አስባለሁ።

23 አይደለም... እኔ—እኔ የምናገረው ወደ ብራናሃም ቤተክርስቲያን ለሚመጡት ብቻ ነው።

24 ማንኛችሁም ውድ ወንድሞች... እንደሚመስለኝ፡ አንዳንዶቻችሁ ጉባኤዎች እንዳሏችሁ፡ አውቃለሁ። ምስኪን ወንድማችን በሴሊስበርግ ነው ያለው፡ የ—የተለያዩ ሰዎችም፡ ጉባኤዎች አላቸው። አሁን፡ ተመልከቱ፡ ጉባኤያቸው የተሃድሶ ነው። እነዚያንም ተከታተሉ። እነዚህ ከዚያ ወጥተው፡ በክፍተት የቆሙ፡ የክርስቶስ ወጣት አገልጋዮች ናቸው። ቤተክርስቲያናቸው እውነትን በካደች ጊዜ፡ እና እንደዚያ ያሉ ነገሮች ሲከሰቱ፡ ወዲያውኑ ትተው ሄዱ። እግዚአብሔርም ወደ አገልግሎቱ ጠራቸው። አዎን፡ ወዳጄ። አ—አንድ በጣም የማደንቀው ሰውዬ አለ... ሰሙ ትዝ አይለኝም። ነገር ግን ወጣት፡ መልካም፡ ቈንጆ-የሆነ፡ እና አንዲት ተወዳጅ ሚሰት እና ልጆች ያሉት ሰው ነው።

25 እ—ሌላውም ወንድም ጁኒ ጃክሰን ነው እሱም አንዳንድ ሰብሰባዎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡ ይህም ሌላኛው አስደናቂ፡ የሆነው የእግዚአብሔር የጸጋው ሽልማት ነው። እና በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ ሪቫይቫል ሲያደርጉ፡ በቀጥታ ወደ እነሱ ሂዱ፡ ምክንያቱም እናንተ... ያ ማድረግ ያለባችሁ ነገር ነው። ምክንያቱም፡ ማን ያውቃል፡ አንድ ኃጢአተኛ ወደ መሠዊያው መጥቶ ሊሆን ይችላል፡ ያንንም ሰው ወደ ክርስቶስ ለመምራት ተፈልጋችሁ ሊሆን ይችላል፡ ይህም በሌላኛው በኩል ታላቅ ሽልማታችሁ ይሆናል።

26 ይህ ቤተክርስቲያንን ለማስተማር እና ለማስተካከል፡ እዚህ ተብርናክል ውስጥ፡ እየረዳን ነው።

27 አሁን፡ ሰዓቴን አላመጣሁም፡ ስለዚህ አንድ ሰው ሰዓት ያይልኛል። ዶክተር እንዳሳየኝ፡ እሱ ሰዓት አለው፡ ስለዚህ፡ ወንድሜ ያይልኛል። ስለዚህ አሁን... [“ዶክተር” ወንድም ኤድጋር ብራንሃምን “ብዙ አላስከፍልህም፡” አለውና፡ ሰዓቱን ለወንድም ብራንሃም ሰጠው—እርታዒ።] ብዙ አታስከፍለኝም? መልካም። መልካም፡ እንግዲህ፡ ምንም ችግር የለውም። መልካም፡ እንግዲህ፡ ከጅምሩ እኔም ክፍያው ልክ ነው ብዬ አላምንም። ስለዚህ... [“አመሰግናለሁ። ስለ አንተ አንድ የምናገረው አለኝ።]” አሁን፡ ኦ፡ ኦ፡ ሽ፡ ሽ፡ ሽ፡ ሽ። [“ዛሬ ጠዋት፡ በልደት ቀኔ፡ አንተን ለማስደሰት፡ አስር ሳንቶሞች አስቀርቼ ነበር።”] እውነትህን ነው? እንግዲያውስ... ይህ ሰዓት በጣም ተሻሽሏል፡ ዶክተር። እኔን

ለማሰደሰት፡ የእርሱ ልደት ላይ፡ አሥር ሳንቲሞች እንዳሰቀረ እየነገረኝ ነው፡ ምክኒያቱም በእኔና በሱ መካከል የሁለት ወይም የሦስት ዓመት ልዩነት አለ። ስለዚህ የት እንደደረሰኩ ማየት ትችላላችሁ፡ መንገድ ላይ ነኝ። ኦህ፡ ይህ ግን፡ ለእኔ፡ ምንም አያሳሰበኝም። አሁን፡ ብዙ አልናገርም አላቆያችሁም።

28 አሁን፡ በደጃችን እንግዶች ካላችሁ፡ በሙሉ ልባችን በደስታ እንቀበላችኋለን። እንኳን ወደዚህች ትንሿ ተበርናክል በደህና መጣችሁ። ብዙ ሕንጻ የለንም። ግንባታ ለማድረግ ዕቅድ ላይ ነን፡ ትልቅ ቦታ አይደለም፡ ነገር ግን... ይህኛው በጣም አርጅቷል። እናም እዚህ ጋር ቄንጆ ትንሽና ምቹ የሆነች ቤተክርስቲያን፡ በተቻለን ፍጥነት... ጌታ ሲፈቅድልን ለመገንባት እንሞክራለን። ለዚህም ብዙዎቻችሁ አስተዋጽኦ እያደረጋችሁ ነው፡ ለዛም በጣም እናመሰግናለን።

29 አሁን ዛሬ ጠዋት፡ አብራችሁኝ 1ኛ ሳሙኤል፡ ምዕራፍ 8ን፡ እንድታነቡ እፈልጋለው፡ ምናልባትም፡ ትንሽ የጽሑፍ አንቀጽ ለማውጣት፡ ከ19ኛው ቁጥር እንጀምር፡ ከ19ኛው እና ከ20ኛው ቁጥር፡ እንጀምር።

30 አሁንም፡ እንደከፈታችሁት፡ እ... እናነበዋለን፡ ከዚያም ወደ ጸሎት እናልፋለን። እና ዛሬ ጠዋት፡ "በጸሎት አስቡኝ" የሚሉ ጥያቄዎች፡ ይኖሩ ይሆን? ከሁለት፡ ወይም ከሦስት፡ ሳምንታት በፊት፡ ባለፈው ሰብሰባችን፡ ሰብሰባ በማደርግበት ጊዜ... እኛ...

31 በነገራችን ላይ፡ ጥቅሱን እያወጣችሁ ሳላችሁ፡ የቻውታኩዋ ሰብሰባ የሚጀምረው፡ በ 6 ነው። በሚድልታውን፡ ኦሃዮ ጥሩ ጊዜ፡ እንጠብቃለን። እናንተ የዕረፍት ጊዜያችሁም እየቀረበ ነው፡ ኑ። በዚያም፡ በወንዙ አጠገብ፡ ትልቅ ጊዜአዊ መጠለያ ይሆናል፡ ኦህ፡ እኛ... የተለያዩ ሰባኪዎችን ትሰማላችሁ። እነዚህ ሁሉ ሰባኪዎች፡ ቀንና ሌሊት፡ በየጠዋቱ፡ በወንዙ አጠገብ ላይ-እና-ታች ይላሉ። ስለዚህ ሁሉም አንድ ላይ ይሰበሰባሉ። ይህ ትልቅ የጊዜአዊ መጠለያ ቦታ ነው፡ ከሲልቨር ሂልስ፡ በብዙ እጥፍ ይበልጣል። እና—ከዚያም ከሰምንት እስከ አሥር ሺህ ሰዎችን መያዝ የሚችል ትልቅ ቦታ አለ። እና ሁሌም በሰው የተሞላ ነው። ኦሃዮ ውስጥ ጥሩ ጊዜ ይኖረናል።

32 እኔም በቀደም ቀን ማለዳ፡ ለሸማግሌው ወንድም ኪዲ፡ ልጸልይለት ሄጄ ነበር። ከሦስት ሳምንታት በፊት፡ የነገርኳችሁን ታስታውሳላችሁ? ዶክተሩ 24-ሰዓት ብቻ፡ እንደሚኖር ነግሮት ነበር። እርሱ አሁን ተነሥቶ እየተራመደ ነው። ሊዘምረው ያልቻለውን መዝሙር፡ ጥቅስ ጠቅሷል። እኔም በቀደም ማለዳ ላይ፡ ወደ ውስጥ ሄጄ እሱን ሰመለከት፡ ትንሽ ፎጣ በላዩ ላይ ነበር። ወደ እርሱ መድረስ እንድችል፡ ከመንጋቱ ከሶስት ወይም ከአራት ሰዓታት በፊት ወጣሁ። የፕሮስቴት ካንሰር እንዳለበትና በዚያው ቀን፣ እንደሚሞት ነግረውኝ ነበር።

33 እና ምስኪኗ፡ ውዷ፡ አሮጊት ሚሰቱ፡ በቀን አምሳ ሳንቲም እየተከፈላት ታጥብ ነበር፡ ይኸውም ባለቤቷን እንደ ሰባኪ መስኩ ላይ ለማቆየት፡ ያለ እረፍት፡ ከንጋት እስከ ማታ ድረስ፡ በሃምሳ ሳንቲም ነው። የሁለት-ሳምንት ሪቫይቫል ይሰብክና፡ መባ ሲቀበል፡ ስማንያ ሳንቲም ያገኛል።

34 በቀደም ጠዋት ግን፡ ሁለቱ ምስኪን ጥንዶች፡ ሸምግለው ቁጭ ብለው አየኋቸው፡ ማለቴ፡ ምስኪን ባልና ሚስት፡ ተቀምጠው፡ ትንሽ ፎጣ ትከሻው ላይ ሆኖ አየኋቸው። እርሱም ከለወጣቸው ሰዎች አንዱ፡ የዘጠና-ሁለት ዓመት

ዕድሜ አዛውንት፡ አስተዋይ እና ብልህ፡ የለየለት ጴንጤቆስጤ ሰው፡ በዚያ ተቀምጧል፡ ታውቃላችሁ። እኔም አልኳቸው፡ “እናንተ ሽማግሌዎች እዚህ ለምን እንደመጣችሁ ታውቃላችሁ? መርከቡ እስኪመጣ ድረስ እየጠበቃችሁ ነው።” በቃ። ሩጫቸው፡ ስኬታቸው ሁሉ፡ ዓ—ዓላማቸውን አሳክተዋል፡ አሁንም ወደ ሽልማታቸው ለመሄድ ዝግጁ ናቸው።

35 እኔም ለወንድም ቼቭ፡ ለወንድም ኪድስን... ኪድ፡ ያን ዕለት ጠዋት፡ “በቻውቶኳ ሰብሰባ ላይ ትሣተፋለህ” አልኩት።

36 እሱም ትናንና ደውሎ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ በዚያ እ... እገኛለሁ፡” ብሎኛል። ደህና ሆኗል።

37 በአብዛኛዎቹ ሰብሰባዎች፡ በአዲሱ አገልግሎቴ ብዙዎች እየሳበ ነው። ይህ ወንድም፡ እዚህ ጋር የቆመው ባፕቲስት ወንድም፡ በአሰራዎቹ-ዕድሜ ላይ፡ የምትገኝ ሴት ልጁ፡ ራሷን መቆጣጠር አትችልም ነበር። እኔም በቀደም ቀን ጥዋት፡ “ልጅህን በጌታ ኢየሱስ ፊት አቅርቤአታለሁ፡” አልኩት። ወደ ቤት በሄደ ጊዜም፡ ድና አገኛት። ሌላም ሊጠመቅ የተዘጋጀ አንድ ሰው ደግሞ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ አለ።

38 ሚስተር. ሶትማን የተባለ፡ ከካናዳ የመጣ፡ አንድ ወዳጄ፡ እማቹ-በሞት-አፋፍ ላይ እያለች፡ “እዚያ-ስትደርስ-እማችህ፡ ደኅና ሆና፡ እያገገመች ታገኛታለህ፡ እሺ፡” አልኩት። እንደዚያም ሆነ። እና ብቻ... ሰዎች እየመጡ ነው። ገና በጨቅላነቱ ነው፡ ላይ እና ታች እያለ ይገኛል። ነገር ግን፡ ኦህ፡ ከሁሉም በላይ እጅግ በጣም፡ ከፍ ያለ ነገር እንጠብቃለን። ያለንበት ዘመን ክፉ እና በመጨረሻው ነው፡ ቢሆንም እጅግ በከበረ ዘመን ላይ ነን።

39 አሁን ደግሞ፡ የሳሙኤል መጽሐፍ 8ኛውን ምዕራፍ ለማንበብ፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ይዛችኋል? ለጁን ቀሪውን ለመቅዳት፡ እዚያ እቆያለሁ ብዬ ቃል ገብቼ ነበር፡ ሰብሰባችንን፡ ገና መጀመራችን ነበር።

> **ሕዝቡ ግን የሳሙኤልን ነገር ይሰማ ዘንድ፣ እንቢ አለ፡ እንዲህ አይሁን፣ ነገር ግን ንጉሥ ይሁንልን፣**
>
> **እኛም ደግሞ... እንደ...** አሕዛብ፡ ሁሉ **እንሆናለን፣ ንጉሣችንም ይፈርድልናል፡ በፊታችንም ወጥቶ፡ ስለ እኛ ይዋጋል አሉት።**
>
> **... ሳሙኤልም የሕዝቡን ቃል** ሁሉ **ሰማ፡ እናም**... **ለእግዚአብሔርም ተናገረ።**
>
> **እግዚአብሔርም ሳሙኤልን፡ ቃላቸውን ሰማ፡ ንጉሥም አንግሥላቸው አለው። ሳሙኤልም የእስራኤልን ሰዎች፡ እያንዳንዳችሁ** ወደ **ከተማችሁ ሂዱ አላቸው።**

40 አሁን ከዚህ ለመምረጥ መሞከር ካለብኝ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች የምናገረውን፡ የመልእክቴን ርዕስ እንዲህ እላለሁ፡ **የተጠላው ንጉሥ** የተሰኘውን ርዕስ፡ መምረጥ እፈልጋለሁ።

41 ይህ ዘመን፡ በዘመናት እንደሆነ ሁሉ፡ ሰዎች አምላክ እንዲመራቸው ያልፈለጉበት ወቅት ነበር። የራሳቸውን የአመራር ስልት መከተል ፈለጉ። እናም ይህን ታሪክ በዚህ ማለዳ... ወደ ቤታችሁ ስትሄዱ፡ ሙሉውን ብታነቡት ጥሩ ነው። ይህ የሆነው በእግዚአብሔር ሰው፡ በነቢዩ፡ በሳሙኤል ዘ—ዘመን

ነው። እርሱም ፍትሃዊና፡ ጥሩ ሰው ነበር፡ የተከበረ፡ መልካም ስም ያተረፈ፡ ለሕዝቡ ታማኝና ሀቀኛ ነበር፡ በፍጹም አታሏቸው አያውቅም፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚለውን ብቻ ይነግራቸው ነበር።

42 ሰዎቹ ግን ይህን ፕሮግራም ለመለወጥ ወደመፈለግ ደረሱ። ፍልስጥኤማውያንን፡ አማሌቃውያንን፡ አሞራውያንን፡ ኬጥያውያንን፡ እና ሌሎችንም የዓለም ህዝቦች ተመለከቱ፡ እነሱም የሚገዟቸውና፡ የሚያስተዳድሯቸው፡ የሚመሯቸው፡ ጦርነታቸውን የሚዋጉላቸው፡ እና ወዘተ ነገሥታት እንዳሏቸው ተገንዝበው ነበር፡ ይህም እስራኤል እነዚህን ነገሥታት እና እነዚህን ሰዎች፡ ለመምሰል የፈለጉ ይመስላል።

43 ይሁን እንጂ፡ በየትኛውም ዘመን፡ የእግዚአብሔር ዓላማ ሕዝቦቹ እንደ ዓለም ሰዎች እንዲመላለሱ፡ ወይም እንደ ዓለም ሕዝብ እንዲተዳደሩ ወይም እንዲቆጣጠሩ አይደለም። የእግዚአብሔር ህዝቦች፡ ሁልጊዜም ቢሆን፡ ወ—— ወጣ ያለ ህዝብ፡ ተጠርቶ-የወጣ፡ ልዩ፡ የተለየ ህዝብ ነው፡ በነገር ሁሉ እጅግ የተለዩ በድርጊታቸው፡ በመንገዳቸው፡ በኑሮአቸው፡ ከዓለም ህዝቦች ሁሉ ይልቅ የተለዩ ናቸው። ለነገሮች ያላቸው ፍላጎት፡ መኳከያቸውም-ሁሉ፡ ሁሌም የዓለም ሕዝብ ከሚፈልገው ነገር ጋር የሚቃረን ነው።

44 እስራኤላውያን ወደ ሳሙኤል መጥተው እንዲህ አሉት፡ “አሁን፡ አንተ አርጅተሃል፡ ወንዶች ልጆችህም የአንተን ምሳሌ አይከተሉም።” ምክንያቱም፡ እንደ ሳሙኤል እውነተኞች አልነበሩም። ጉቦኞች እና ገንዘብ ተቀባዮች ነበሩ። እነሱም እንዲህ አሉት፡ “ሳሙኤል፡ ልጆችህ እንደ አንተ አይደሉም፡ ስለዚህ ወጥተህ ንጉሥ እንድታነግሥልን፡ እርሱንም እንድትቀበው፡ እኛንም እንደ ሌሎች ዓለማውያን ህዝቦች እንድታደርገን እንፈልጋለን።”

45 ሳሙኤልም ይህ እንደማይሳካላቸው ሊነግራቸው ሞከረ። እንዲህም አላቸው፡ “ይህን ካደረጋችሁ፡ መጀመሪያ ታውቃላችሁ፡ ልጆቻችሁን በሙሉ ከቤታችሁ እንደሚያስወጣ፡ በሰረገሎቹ ፊት እንዲሮጡ፡ የጦር ትጥቅና ጦር እንዲይዙ፡ ወታደሮች እንደሚያደርጋቸው እወቁ። ይህ ብቻ ሳይሆን፡ ዳቦ እንዲጋግሩ፡ ሠራዊቱን እንዲመግቡ፡ ሴት ልጆቻችሁን፡ ከእናንተ ይወስዳቸዋል። እና፡” እንዲህ አላቸው፡ “ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ፡ ከእህላችሁ፡ ከገቢያችሁ ሁሉ፡ የተወሰነ ግብር ይወሰዳል። የተወሰኑ የመንግሥት ዕዳዎችን፡ እና የመሳሰሉትን፡ መክፈል ስላለበት፡ ሁሉንም ግብር ያስከፍላል።” “እናንተ፡ ሙሉ በሙሉ፡ ስሕተት እየሠራችሁ ነው ብዬ አሰባለሁ፡” አላቸው። ነገር ግን...

46 ሕዝቡም “አሁንም ግን እንደሌሎች ሕዝብ መሆን እንፈልጋለን፡” አሉት። ወንዱም ሴቱም እርስ በርሳቸው እንዲመሳሰሉ የሚመኙት አንድ ነገር አላቸው። በምድርም ላይ አርአያችን ሊሆን የኖረ አንድ ሰው ብቻ ነበር፡ እርሱም ለሁላችን የሞተው፡ ጌታችን እና አዳኛችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እኛ ምን መሆን እንዳለብን ፍጹም አርአያ ነበር፡ ሁል ጊዜም የአብን ፍቃድ የሚያደርግ፡ ትክክል የሆነውን ብቻ የሚያደርግ ነው።

47 ሳሙኤልም ሕዝቡን ለማሳመን የቱንም ያህል ቢሞክር፡ ቀንም ሆነ ሌሊት ያለማቋረጥ፡ ይጠይቁት ነበር፡ “ንጉስ እንፈልጋለን። ሰው እንፈልጋለን። ‘ይህ የእኛ መሪ ነው፡’ ማለት የምንችልበትን ሰው እንፈልጋለን።”

48 ይህ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ አያውቅም። ሰዎች አንዳቸው በሌላው ላይ እንዲገዙ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ አያውቅም፡ ወደፊትም ቢሆን ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ይገዛል። እግዚአብሔር ገዢያችን፡ ንጉሣችን ነው።

49 እና ዛሬ ደግሞ፡ በጣም እጅግ የከፋ ነው፡ ምክንያቱም ዛሬም ሰው ተመሳሳይ አሳብ ያለው ይመስላል። ሰው ሰውን በመግዛት ፈንታ፡ አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ሰውን እንደሚገዛ መረዳት የቻሉ አይመስሉም።

50 በመሆኑም የቂስ ልጅ የሆነውን፡ ሳኦልን ለራሳቸው መረጡ። እሱም ታማኝ ሰው ነበር፡ የተከበረ ሰው። ለዚያ ሕዝብ ግን ልካቸው ነበር፡ ምክንያቱም እርሱ ታላቅ፡ ረዥም፡ እና የተከበረ፡ ጠንካራ ሰው ነበር። ቅዱስ መጽሐፍ ከማንኛውም እስራኤላዊ በላይ ከራሱ እና ከትከሻው በላይ የሚረዝም ነበር ይለዋል። ንጉሣዊ-መልክ ነበረው፡ ፊቱም የሚያምር ነበር። ብልህና ልዩ ሰው ነበር።

51 አሁን፡ በዛሬው ጊዜም ሰዎች የሚመርጡት እንዲህ ዓይነቱን ሰው ነው። ሕዝቡ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን መንፈስ ቅዱስ እንዲመራት፡ እና እንዲቆጣጠራት በማድረጉ ደስተኛ አይመስሉም። የሆነ አካል፡ የሆነ ሰው፡ የሆነ የሃይማኖት ተቋም፡ የተወሰኑ ሰዎች ቤተክርስቲያንቷን እንዲመሩ ይፈልጋሉ። ራሳቸውን፡ ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር እጅ አሳልፈው መስጠት፡ መንፈሳዊ መሆን፡ በመንፈስ ቅዱስ መመራት አይችሉም። የሆነ ሰው ሃይማኖታቸውን እንዲያከናውንላቸው ይፈልጋሉ፡ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው እና ሁሉንም ነገር፡ የሚነግራቸው ሰው ይፈልጋሉ።

52 ስለዚህ ይህ ሰው ለቦታው በትክክል የሚመጥን ይመስላል፡ ምክንያቱም በጣም ምሁር ሰው ነበር።

53 ዛሬም በብዙ ነገር ተመሳሳይ ነው። እኛም ቤተክርስቲያናችንን እንዲቆጣጠሩ፡ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዲቆጣጠሩ፡ እንደነዚህ ያሉ ሰዎችን፡ መምረጥ እንወዳለን። እሱን ለመቃወም ምንም የምናገረው ነገር የለኝም፡ ነገር ግን፡ እዚህ ጋር ማንሳት የምፈልገው ነጥብ፡ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ የአይደለም፡ አልነበረም፡ ወደፊትም እንደዚህ ያለ ነገር፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ግለሰብ ይገዛል፡ ሕዝቡንም ይገዛል።

54 ከዚያም ይህ የቂስ ልጅ፡ ታላቁ ሰው፡ ቁመናው፡ እና—እና ሁሉም ነገሩ፡ ለሕዝቡ የሚመጥን ይመስል ነበር፡ ካባው በእሱ ላይ ድንቅ ይመስል ነበር፡ አክሊሉም በራሱ ላይ ያምር ነበር፡ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ በላይ ከፍ ብሎ ይታይ ነበር፡ ሲንጎራደድም፡ ለእስራኤል መንግሥት እ—እውነተኛ ሀብት ይመስል ነበር። ምክንያቱ፡ የሌሎች ሀገራት፡ ነገሥታት ሲያዩት፡ "እንዴት ያለ ሰው ነው!" ብለው ያስቡ ነበር፡ በጣታቸው እየጠቀሙ እንዲህ ይሉታል፡ "እንዴት ያለ ታላቅ ንጉሥ እንዳለን፡ ተመልከቱ! በላያችን ያለውን ታላቅ ሰው ተመልከቱ!"

55 ለማለት ያሳዝናል ግን፡ ዛሬ በቤተክርስቲያንቷ ውስጥ ይህ ምን ያህል እውነት ነው፡ እንደዚህ ለማለት ይወዳሉ፡ "ፓስተራችን ጠባብ-አስተሳሰብ ያለው ሰው አይደለም። እሱ ታላቅ ሰው ነው። ከሃርትፎርድ ተመርቋል፡" ወይም ከሌላ ታላቅ ስነመለኮት ትምህርት ቤት። "**ከዚህ-እና-ከዚያ** አራት ዲግሪዎች

አሉት። እና በሰዎች መካከል በጣም ተግባቢ ሰው ነው።" ያ ሁሉም መልካም ሊሆን ይችላል፡ የራሱም ቦታ አለው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ለቤተክርስቲያኑ ግን በመንፈስ ቅዱስ፡ እና በመንፈሱ መመራት ነው።

56 ነገር ግን እንዲህ ማለት ይወዳሉ፡ "የትልቅ ሃይማኖት ተቋም አባል ነን። ገና ከምስረታ ጀምረን ነበርን፡ እናሳ በነበርንበት፡ በጣም ጥቂት ሰዎች በነበርንበት፡ እና ትንሽ ሆነን ነበር የጀመርነው። አሁን ግን ካሉት ትላልቅ ሃይማኖት ተቋሞች መካከል አንዱ እስከምንሆን ድረስ አድገናል። እጅግ በጣም ጥሩ ትምህርት ቤቶች፡ እጅግ በጣም የተማሩ አገልጋዮች አሉን። እጅግ በጣም ጥሩ-አለባበስ ያላቸውም ሰዎች አሉን። በከተማዋ ውስጥ አሉ የተባሉ ምሁራን በሃይማኖታችን ይታደማሉ። እንዲሁም ለበጐ አድራጎት እንሰጣለን። እንዲሁም መልካም ሰራዎችን እንሠራለን፡ እነዚህንም ሁሉ እናደርጋለን።" እኔንም እንዲህ አይነቱ፡ ምንም ቃል እንዳልናገር፡ እግዚአብሔር ይጠብቀኝ፡ ምክንያቱም ያ ሁሉ መልካም ነው።

57 ቢሆንም፡ ግን፡ ሰው ሰውን እንዲገዛ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። እግዚአብሔር በጴንጤቆስጤ ዕለት፡ የሰውን ልብ፡ እና ሕይወቱን እንዲገዛ፡ መንፈስ ቅዱስን ላከ። ሰው ሰውን እንዲገዛ አልተፈጠረም።

58 እንዲህ መናገር ግን ያምረናል። እንዲህ ዓይነት ታላቅ ድርጅት አባል መሆናችንን መናገራችን ኩራት ይሰማናል።

59 "ክርስቲያን ነሽ? " በሆስፒታል ሳለሁ፡ በዚህ ርዕስ ላይ የተሰማኝ ይህ ነበር። "ክርስቲያን ነህ፡" እያልኩ እጠይቅ ነበር?

"**የዚያ-እና-የዚያ** አባል ነኝ።"

"ክርስቲያን ነህ? "

"**የዚያ-እና-የዚያ** አባል ነኝ።"

60 እንዲትም ነርስ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበብኩ ወደነበርኩበት፡ አልጋ ጠጋ አለች፡ በ——ቦታው አዲስ ነርስ ነች። እሷም "ጤና ይስጥልኝ፡" አለችኝ። "ሬርቨረንድ ብራንሃም ትመስለኛለህ፡ የመጣኹው አካላዊ-ምርመራ ለማድረግ ነው፡" አለችኝ።

እኔም "አዎ ነኝ፡" አልኳት።

61 እሷም እንዲህ አለችኝ፡ "ትንሽ እንዲሻልህ ለማድረግ፡ ጀርባህን በዚህ አልኮል ማሸት እችላለሁን? "

እኔም "ማድረግ ትችያለሽ፡" አልኳት።

62 እሷም ጀርባዬን እያሸችኝ፡ "የየትኛው ሃይማኖት ተቋም አባል ነህ፡" አለችኝ?

63 እኔም "ኦህ፡ እኔ በጣም ጥንታዊ የሃይማኖት ተቋም አባል ነኝ፡" አልኳት።

እሷም "እሱ የትኛው ሃይማኖት ነው፡" አለችኝ?

64 እኔም "ገና ዓለም ሳይደራጅ የተደራጀች ናት፡" አልኳት።

65 እና "ኦህ፡" አለች፡ "እንጃ? ያንን የማውቀው አይመስለኝም፡" አለችኝ። "እኔ **እከሌ** የተባለውን ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ። የእሱ ተቋም ነህ እንዴ፡" አለችኝ?

66 እኔም፡ “አይ፡ እመቤት። እሱ ተቋም የተደራጀው፡ ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት ነው። ይሄኛው ግን የጀመረው ያኔ ገና የንጋት ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩና፡ ሰዎችን ሁሉ የሚያድን አዳኝ መምጣቱን ሲመለከቱ፡ የአምላክ ልጆች በደስታ ሲጮኹ ነበር” አልኳት።

67 እሷም ጀርባዬን ማሸት አቆመች። እና እኔም እንድታሸኝ፡ **እንደዚህ**፡ ትንሽ ጎበጥ ብዬ ነበር። እሷም ከዚህ፡ ከኮሪደን አከባቢ ነው የመጣችው። ማውራት ቀጠልን። እሷም እንዲህ አለች፡ “ወዳጄ፡ እኔ ሁሌም ይህን አምናለው እግዚአብሔር አምላክ ከነበረ፡ እርሱ፡ ዛሬም ቢሆን፡ ልክ እንደ ድሮው ዘመን አምላክ ነው።” “ቤተ ክርስቲያኔ ይህንን በግልጽ ብትክደውም፡ እኔ ግን እውነት ነው ብዬ አምናለሁ፡” አለችኝ።

68 እኔም “እንቺ ወጣት ሴት፡ ከእግዚአብሔር መንግሥት ብዙም አልራቅሽም፡” አልኳት።

እሷም “ፈዋሽ ከነበረ፡ አሁንስ ፈዋሽ አይደለምን፡” አለችኝ?

እኔም “እርሱ በእርግጥም አሁንም ፈዋሽ ነው፡ እህቴ፡” አልኳት።

69 ሰው ግን ሰውን መግዛት ይፈልጋል፡ ሌላውን ሰው መግዛት ይፈልጋል። ሰውም ሰው እንዲገዛው ሰው ይፈልጋል። እግዚአብሔር እንዲገዛው አይፈልግም።

70 ስለዚህ ይህ፡ ሳኦል የሚባለው፡ የቂስ ልጅ፡ ለፈለጉት ነገር መልስ ብቻ ነበር፡ ታላቅና ግርማ ሞገስ ያለው ሰው ነበር። እና... ኦህ፡ ወደ ጦርነታቸው፡ ወደ ሌላም ነገር ሊመራቸው ይችላል። አሁንም፡ ግን፡ እግዚአብሔር ነገሮችን የሚያከናውንበት መንገድ ያ አልነበረም። እግዚአብሔር የፈለገው ያ ታማኙ ሽማግሌው ነቢይ እንዲመራቸውና፡ ቃሉን እንዲነግራቸው ነበር።

71 አሁን፡ ዛሬ፡ በምንኖርበት በታላቁ፡ የቤተክርስቲያን ዘመን፡ እኛም፡ በትክክል፡ እግዚአብሔር እንድናደርግ ከሾመን ነገር በተቃራኒው-መንገድ-ሄደናል ይህን በሙሉ ልቤ አምናለሁ። የአዳኛችን የኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻ ቃላት በማርቆስ 16። እንዲህ ይላል፡

**ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፡ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።**

**ያመነ የተጠመቀም ይድናል፡... ያላመነ ግን ይፈረድበታል።**

**ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፣ በስሜ** አጋንንትን **ያወጣሉ፣ በአዲስ** ቋንቋ **ይናገራሉ፣**

**እባቦችን ይይዛሉ፡** ወይም... **ቢጠጡ... የሚገድልም** ነገር **ቢጠጡ፡** አይጎዳ**ቸውም፥** እጃቸውን **በድውዮች...** ላይ ይጭናሉ**፡... እነርሱም ይድናሉ።**

72 ከመንፈስ ቅዱስ አመራር ውጭ፡ ማንም ሰው፡ የቂስ ልጅም ቢሆን፡ ይህን ሊያፈራ የሚችል አንድም ሰው የለም። ነገር ግን ለመርካት፡ እና እንደ ሌላው ዓለም ለመምሰል፡ ትምህርት ቤቶችን ሠርተናል፡ ሴ—ሴሚናሪዎችን ሠርተናል፡ እና ድርጅቶችን ሠርተናል።

73 አሁን፡ ይህች ሀገር መሪዋ መንፈስ ቅዱስ ነበር። ይህች ሀገር የነፃነት አዋጇን ከፃፈችበት ጊዜ ጀምሮ... የሚመራት ገዢ ነበራት። እና አንድ ተጨማሪ

ወንበር በዚያ ያስቀምጡ ነበር። ከእግዚአብሔር ልጅ በቀር በዚያ ጠረጴዛ ላይ ሌላ ነገር እንደማይቀመጥባት በአእምሮዬ ውስጥ አንድም ጥርጣሬ የለም፡ ይህች ሀገር የተመሰረተችው በሃይማኖት ነፃነትና ለሁሉም ነጻነት መርሆዎች እንዲሁም፡ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ቃል ላይ በመመስረት ነው።

74 ያ ግን አሁን አበላሽተነዋል። በፖለቲካው፥ በሐሰተኛ ቃል ኪዳኖችና፡ በመግዛትና በመሸጥ፡ የተመሰረቱ ሰዎች መርጠናል። እስከ... አገራችን፡ ፖለቲካችንና፡ ዴሞክራሲያችን፡ ከኮሚኒዝም እና ከሌሎች ከማንኛውም ዓይነት ኢዝም ጋር እ—እስኪቀላቀል ድረስ ያንን አድርገናል።

75 እናም ብዙ ጊዜ የጸሎት ክፍል ጊዜዎች እናደርጋለን፡ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ስብሰባ፡ እና ሌላ... ወይም ውይይት በሚኖር ጊዜ ይጸለያል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፡ ረዘም ላለ ጊዜ፡ ለጸሎት ጥሪ የተደረገበት፡ አንድም ጊዜ እንኳን አልነበረም። ያለ ጸሎት ልዩነቶችን እንዴት ልንፈታ እንችላለን? በመላው ዓለም፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ አመራር ማንኛውንም ነገር እናደርጋለን ብለን፡ እንዴት ማሰብ እንችላለን?

76 ነገር ግን ለአገራችን ለስንደቅ ዓላማዋና ለምትወክለው ሪፐብሊክ፡ በፍቅርና በአክብሮት እንዲህ እላለሁ፥ መሪያችንን፡ መንፈስ ቅዱስን አስወግደናል፡ እንዲሁም ብልሹ በሆነ ፖለቲካ አማካኝነት ብልሹ አስተሳሰብ ያላቸውን ሰዎች አምጥተናል። ካልተጠነቀቃችሁ፡ እስካሁን ካደረጓቸው እጅግ አስከፊ ስህተቶች መካከል፡ አሁኑኑ ይፈጽማሉ፡ ምክንያቱም ሕዝቡ በሰው መገዛት ስለሚፈልግ ነው።

77 በዚህ በዩናይትድ ስቴትስ ዋና ከተማ፡ በፕሬዚዳንትነት፡ በኮንግረስ፡ እና በፍትህ አዳራሾቻችን ውስጥ የሚያስፈልጉን፡ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ፡ እና በመለኮታዊው መመሪያ የሚመሩ ሰዎች ናቸው። በአንጻሩ ግን፡ እኛ የምንመርጠው፡ ብልሃት ያላቸው፡ “የአምልኮ መልክ ያላቸው፡ እና የእግዚአብሔርን ኃይል የሚክዱ፡” አምላክ የለሽ የሆኑ ሰዎችን ነው፡ አንዳንዴም ከዚህም የከፉ ሰዎችን፡ ወደ ህዝባችን፡ ወደ ፖለቲካው ግዛታችን አምጥተናችኋል።

78 ይህ ብቻ ሳይሆን፡ በቤተክርስቲያናችንም ያው ነው። አብያተ ክርስቲያናችን የተበላሹት፡ እረኞቻችንን ስንመርጥ፡ ወደ ሴሚናሪዎቻችን ሄደን እጅግ የላቁ ሰዎች ታላላቅ ምሁራንን፡ በጣም ብሩህ አስተሳሰብ ያላቸውን፡ ስኮላርሺፕ ያላቸውንና፡ በሕዝቡ መካከል ጥሩ መግባባት ያላቸውን ሰዎች፡ በአካባቢያችን ያሉ ታላላቅ ሰዎችን መርጠናቸዋል፡ ይህን ተቃውሜ የምለው ምንም የለኝም። በመንገዳቸው ደግ የሆኑ፡ በኑሮአቸው ጠንቃቃ የሆኑ፡ በሌሎች ሰዎችና በህዝቦች መካከል፡ በሌሎች ሰዎች መካከል ራሳቸውን በደንብ የሚገዙ፡ በሥራቸው ታላቅ ሰዎች፡ እኔም ክፉ ነገር የማላወራባቸው ሰዎች ናቸው። መንፈሴ ይህን ያህል ክፉ እንዳይሆን እግዚአብሔር ይጠብቅልኝ። አሁንም፡ ግን፡ እግዚአብሔር ለእኛ የመረጠው ያን አይደለም።

79 የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ነው፡ ክርስቶስ በሰዎች ልብ ውስጥ ነው። በመድረኮቻችን ከሚቆሙት ከነዚያ ምሁራን አብዛኛዎቹ የመንፈስ ቅዱስን ህልውና ይክዳሉ። አብዛኛዎቹ መለኮታዊ ፈውስን እና የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መኖርን ይክዳሉ።

80 ትናንት፡ አንድ ጽሑፍ እያነበብኩ ነበር፡ ከጃክ ኮይ ተከታታይ ከጋዜጣ ቁራጮች አንዱ ነው፡ ብዬ አምናለሁ፡ ሟቹ ጃክ ኮይ፡ ወ... ወደ ጌታ ኢየሱስ ከቀየርኳቸው ሰዎች አንዱ፡ በዘመኑ፡ ታላቅ የጀግንነት ሰው ነበር። በፍሎሪዳም ውስጥ ለጥያቄ ቀርቦ ነበር፡ ምክንያቱም አንድ ትንሽ ልጅን የእግሮቹን እንዲደግፍ የተገጠመለትን ብረቶች፡ እንዲያወልቅ፡ እና በመድረክ ላይ እንዲራመድ ስለጠየቀ ነው። ይህንም ሲያደርግ፡ ልጁ በመድረኩ ላይ፡ ሳይወድቅ ሄዴ፡ ወደ እናቱም ሲደርስ ግን ወደቀ። ይህ ሁሉ የክርስቶስ ጠላት ያዘጋጀው ማታለያ በመሆኑ፡ ይህች ወጣት እና ባለቤቷ ጀግና ወንድማችንን ወደ አገሪቱ ፍርድ ቤት አመጡት።

81 እናም እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን ከወንድም ጃክ ጐን መቆም ሲገባው፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም የሚጠራ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ሰው በጀግንነት፡ ከጐኑ መቆም ሲገባው፡ የጌታን የኢየሱስን ስም የሚጠራ ሁሉም ሰው በጸሎት መንበርከክ ሲገባው፡ ነገር ግን፡ በምትኩ፡ በጋዜጦቹ አርእስተ ዜና ላይ፡ ከታላላቆቹ የሃይማኖት ተቋማት መካከል አንዱ ወንድም ጃክ ኮይን ለመኮነን፡ እና ለማሰር፡ የፈጣሪ መኖር ከማያምኑ ጋር ወግነዋል ይላል። ራሳቸውን የክርስቶስ ስም እያሉ የሚጠሩት ቤተ ክርስቲያን፡ በሙሉ ልቡ ለመጽሐፍ ቅዱስ ለመቆም፡ የሚሞክረውን፡ የእግዚአብሔር ሰው ለመኰነን የፈጣሪ መኖር ከማያምኑ ጋር እንደሚተባበሩ መገመት ትችላላችሁን? እነርሱ ግን አደረጉት።

ከዚያም ወንድም ጎርደን ሊንሴይ ሊያበረታው በዚያ ተገኘ።

82 እና የማያምነው ዳኛ እስዲህ ባለ ጊዜ፡ “ይህ ሰው አጭበርባሪ ነው ምክንያቱም ከዛ ሕፃን እግሮቹን ለመደገፍ የተገጠሙትን ብረቶቹን አውልቆ በመድረኩ ላይ እንዲራመድ አድርጓል፡ እርሱም ‘ተፈውሷል’ ብሏል። ዋሽ፡ ከዶክተሩም ትእዛዝ ጋር የሚቃረን ነገር አደረገ፡ ስለሆነም በማጭበርበር ክስ ተከሷል።”

83 አቶ. ኮይም ተነሥቶ፡ እንዲህ አለ፡ “ጌታዬ፡ ያንን አሳብ እቃወማለሁ። እግዚአብሔር ልጁን ፈውሶታል።”

84 ዳኛው እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔር ያንን ልጅ በመድረኩ አንድ ጫፍ ላይ ፈውሶ በሌላኛው ጫፍ ላይ እንዲታመም የሚያደርግ ከሆነ፡ በዚህ ፍርድ ቤት ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው፡ ይህ ንግግር እውነት ሊሆን ይችል እንደሆነ እጠይቃለሁ። ያ ንግግር በመጽሐፍ ቅዱስ ሊረጋገጥ የሚችል ከሆነ፡ አቶ ኮይ ለንግግሩ መብት አለው።”

85 አንድ አገልጋይ እጁን አነሣና፡ “ክቡርነዎ፡ ጌታዬ፡ መናገር እችላለሁን፡” ጠየቀ?

ዳኛውም “ተናገር፡” አለው።

86 አገልጋዩም ተነሥቶ፡ እንዲህ አለ፡ “በአንድ ምሽት፡ በሚናወጥ ባሕር መካከል፡ አንድ ትንሽ መርከብ ወደ ታች ልትሰጥም በነበረበት ጊዜ፡ የመዳን ተስፋ ሁሉ ጠፍቶ ነበር። ከዚያም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ፡ በውኃ ላይ እየተራመደ፡ ሲመጣ አዩ። ከሐዋርያቱ አንዱ፡ የሆነው ጴጥሮስ፡ ‘ጌታ ሆይ፡ አንተ ከሆንክ፡ በውኃው ላይ እየተራመድኩ፡ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ’ አለው።” እርሱም፡ “ጌታም ለሐዋርያው ጴጥሮስ፡ ‘ና’ አለው። እርሱም

ከጀልባው ወጣ፡ ጌታዬ፡ ልክ እንደ ኢየሱስ ተራመደ፡ በውኃ ላይ ተራመደ። ነገር ግን መፍራት ሲጀምር፡ ወደ ኢየሱስ ከመድረሱ በፊት መስመጥ ጀመረ" አለው።

ያን ጊዜ ዳኛው "ክሱ ተዘግቷል፡" አለ።

የመንፈስ ቅዱስ ምሪት እንጂ፡ የምሁር ሰው አመራር አያስፈልገንም።

87 የቂስ ልጅ፡ ሳኦል፡ በሕዝቡ ላይ አለቃ ሆኖ ተሾመ፡ እርሱም ሁለት ሺህ ሰው ወሰደ፡ ዮናታንም አንድ ሺህ ሰው ወሰደ። ዮናታንም ወደ አንድ የጦር ሰፈር ወርዶ ብዙ የአሞናውያንን፡ የአሞናውያንን፡ ቡድን ገደለ። እርሱም በ—በመታቸው ጊዜ፡ ሳኦል፡ መለከት ነፋ፡ እንዲህም አለ፡ "ሳኦል ያደረገውን አይታችኋል።" ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ጀመረ።

88 ልክ አንድ ሰው ታላቅ የመለኮት ዶክተር መሆን ሲጀምር፡ ወይም ከሰሙ በስተጀርባ ትንሽ ነገር ሲያገኝ፡ ይብዛም፡ ይነስ፡ ሁሉንም-አዋቂ-ይሆናል።

89 የእግዚአብሔር ሰው ትሑት ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች ትሑት ሰዎች ናቸው። መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል የሚሉ ሰዎች፡ ራሳቸውን የተለየ ሰፍራ መስጠት ሲጀምሩ ስታዩ፡ እምነት የሌላቸው፡ ይመስላሉ፡ እየዞሩ፡ ያልሆኑትን ነገር ለመሆን ሲሞክሩ፡ ይህን አትርሱ፡ ጌታ ኢየሱስን እንዳልተቀበሉ እወቁ።

90 ከዚያም ጠላት እንደገባባቸው እናውቃለን። እርሱም ወደ ትንሿ የእግዚአብሔር መንጋ ይገባል፡ ያን ጊዜ የሰውን ሁሉ ቀኝ ዓይን ጎልጉሎ ያወጣል።

91 ጠላት ሁል ጊዜ ለማድረግ የሚሞክረው ያንን ነው፡ ከቻለ፡ ሁለቱንም ዓይኖች ጎልጉሎ ማውጣት ነው፡ ይህም ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር ማየት እንዳይችሉ ነው። ሰይጣን ዛሬ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ላይ ሊያደርገው የሚሞክረው ይህንኑ ነው፡ መንፈሳዊ እይታውን ጎልጉሎ ያወጣውና፡ የሚመራውን የመንፈስ ቅዱስን ስሜት ሳይሆን፡ የአዕምሯዊውን ስሜት ብቻ እንዲከተል ያደርገዋል።

92 ይህን ካደረጉ በኋላ፡ ታላቅ ድል በመጣ ጊዜ፡ ሳኦል ሁለት ታላላቅ በሬዎችን አርዶ ለሕዝቡ ሁሉ ላከ። ይህንን ልብ ብላችሁ እንዲትመለከቱ እመኛለው፡ ሳኦል የበሬዎቹን ስጋ፡ ወደ እስራኤል ሁሉ በመላክ፡ "ሳሙኤልንና ሳኦልን የማይከተል ሰው ሁሉ፡ **ይህ** በሬ፡ እንደሚሆነው፡ ይሁን" አለ። ራሱን ከእግዚአብሔር ሰው ጋር ለማወዳደር ማቅረቡ ምን ያህል አታላይ እንደሆነ አያችሁ? ምን—ምን ያህል ክርስቲያናዊ ያልሆነ ድርጊት ነበር! የሕዝቡ ፍርሃት በሳሙኤል ምክንያት ነበር። ሳኦል ግን ሕዝቡ ሳሙኤልን ስለፈሩ ሁሉም እንዲከተሉት አደረገ። "ከሳሙኤል **እና** ከሳኦል በኋላ እንዲመጡ አድርጓቸው።"

93 ዛሬም እንደዚህ ሲሉ፡ ስንት ጊዜ፡ ሰምተናል! "እኛ ታላቅ ቤተክርስቲያን ነን። እኛ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ነን። እኛ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነን። እ—እኛ **እንደዚህ-እና-እነደዛ** ነን።" ይህም ሰዎች እንዲፈሩ፡ በእውነቱም እግዚአብሔር የሚሠራበት ቦታ ነው ብለው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። የመንፈስ ቅዱስንም አመራር አይፈልጉም። የራሳቸውን የግል ሕይወት መኖር ስለሚወዱ፡

እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች መከተል ይመርጣሉ። ማመን የፈለጉትን ነገር ማመን ይወዳሉ።

94 አያችሁ? መንፈስ ቅዱስ ፈራጃችን ነው። እግዚአብሔር ጳጳስ፡ ወይም ቢሾፕ፡ ወይም ሌላ ሰው፡ ዳኛ እንዲሆን አይሰጠንም። በመንፈስ ቅዱስ መልክ የተገለጸው፡ የእግዚአብሔር አካል የሆነው፡ መንፈስ ቅዱስ ዳኛችንና መሪያችን ነው። አሁን፡ ይህ የሆነው ለምንድን ነው?

95 አባካችሁ ይህ ክብር የጐደለውና በጣም ክብር የጐደለው አባባሌን ይቅር በሉኝ። እንደዛ ማለቴ አይደለም። በፍቅር ነው የምናገረው።

96 ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሴቶቻችን ፀጉራቸውን መቍረጥ ስሕተት እንደሆነ ይናገራል። ሴቶች ሱሪዎች እና ቁምጣዎች መልበስ፡ ከንፈሮቻቸውንና ፊታቸውን ቀለም መቀባት ስሕተት ነው። መንፈስ ቅዱስ ስህተት ነው ይላል።

97 ይሁን እንጂ፡ "እኔን እና ሳሙኤልን እስከተከተልን ድረስ" ምንም ችግር እንደሌለው ሰዎች እንዲነግሩን እንፈልጋለን። ሰድስት ቀናት፡ እንደ ፈለጉ ፈንጭተው፡ እሁድ ጠዋት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ ይወዳሉ። ብዙ የኮሌጅ ዲግሪዎች ያሏቸው እጅግ የተማሩ ምሁራን አነሰ ያለች ሰብከት ብትናገሯቸው… ቀልዳ ቀልድ ጣል ብታደርጉላቸው፡ ልክ እንደ ፊልም ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም፡ ጆሮአቸውን ይኮረኩራቸዋል ያስቃቸዋል። ከዚያ በኋላ ጥቂት ጸሎት ታደርጉላቸዋላችሁ፡ እና ደስታቸውን-በጠበቀ መ—መልኩ ሃይማኖታቸውን እንደፈጸሙ እንዲሰማቸው በማድረግ ቤታቸው ትልኳቸዋላችሁ። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ አይደለም።

98 መንፈስ ቅዱስ በሳምንቱ ውስጥ በየቀኑ እና በየምሽቱ፡ እራሳችሁን ከዓለም ነገሮች በመለየት፡ እግዚአብሔርን በመምሰል እንድትኖሩ ይፈልጋል።

99 ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያኒቱ ይህን አትፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስን መሰማት በሚፈልጉበት መንገድ መተርጐም የ—የሚችል ሰው ይፈልጋሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል የሚናገረውን የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ መሰማት አይፈልጉም። ብዙዎቹ "የተአምራት ዘመን አልፏል፡" ለማለት ይፈልጋሉ። ህዝቡን የሚኮረኩረውም ያ ነው። "የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የለም፡" ለማለት ይፈልጋሉ። ሕዝቡ ከሌላ ዓለም በተለየ መንገድ ምንም እርምጃ መውሰድ አይፈልግም። ወንዶች ፊታቸው ታጥቦ ከ—ከንጹህ ከፊት ገጽታ ጋር፡ አፋቸው ላይ ሲጋራ ጠፍቶ፡ ሳያጨሱ፡ ሺሻ ሳይጠቀሙ፡ ወንዶች የ—የሚያደርጉትን ነገር ሳያደርጉ፡ ወ—ወደ መንገድ መውጣት አይፈልጉም። ሴቶችም ፀጉራቸውን በጣም አጭር አድርገው መቆረጥ፡ እና—ትንሽ ቀሚስ መልበስ፡ ቅርጻቸውን፡ እና የፈልጉትን ነገር ማሳየት ይፈልጋሉ። "ምንም ችግር የለውም፡" የ—የሚሏቸውን ሰዎችን ይፈልጋሉ።

100 ከዚያም፡ በቀደም ምሽት፡ በእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ላይ ሰለ ሰበክኩ፡ አንድ ሰው መጥቶ እንዲህ ሲል ነገረኝ፡ አንድ ትልቅ የሃይማኖት ተቋም፡ አምስት የሚሆኑ ሰዎች፡ እንዲህ አሉ "ወንድም ብራንሃምን እናሰወግዳለን፡ ከእሱ ጋር በምንም አንተባበርም። ወይም እነዚያን ቴፖች መልሳቸው፡ ሰለእነሱም ይቅርታ ትጠይቃለህ፡ ወይም እናወግዝሃለን።"

101 እኔም አልኳቸው፡ "ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እቆማለሁ። በሕይወቴ ውስጥ ያለኝን ሁሉ ቢወሰድብኝም፡ ከቃሉ ጋር እቆማለሁ። እና… "

“ቆይ፡ **ይህን-እና-ያንን** ቴፕ ማጥፋት አይገባህም፡” ብለው ጠየቁኝ?

102 እኔም አልኳቸው፡ “በሕይወቴ፡ ያማፍርበትን ነገር ሰብኬ አላውቅም። እኔ አንድም ቴፕ ይሁን ቅጂዎችን አላጠፋም። እኔ መንፈሰ ቅዱስ ከሚለው ጋር እጸናለሁ። መኖሪያም መሞቻዬም ይህ ነው” አልኳቸው። አሁን ስለራሴ ለመናገር እየሞከርኩ አይደለም። ነገር ግን እናንተ ምን እየተካሄደ እንዳለ ማየት እና መረዳት እንድትችሉ፡ በምሳሌ ለማስረዳት እየሞከርኩ ነው። ሰዎች በሰዎች መመራት ይፈልጋሉ።

103 ሳሙኤልን አልፈለጉትም። ከዚያም ሳሙኤልን ንጉሥ አድርገው ከመቀባታቸው በፊት... ይቅርታ፡ ወይም ሳኦልን፡ ከማንገሳቸው በፊት፡ ሳሙኤል እንደገና ወደ እነሱ መጣ። እኔም እሱ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ሊናገረው በሚችል ቋንቋ እንዲህ እላችኋለሁ። ልታነቡት ትችላላችሁ። “እግዚአብሔር ንጉሣችሁ ቢሆን ክፋቱ ምኑ ጋር ነው፡ ብሎ ጠየቃቸው?

“እንግዲህ፡ እግዚአብሔርን አናየውም።”

104 “እንግዲያውስ፡ እኔ የእርሱ ተውካይ ነኝ፡” ሳሙኤልም፡ “የተሳሳተ ነገር ነግርያችሁ አውቃለሁን? በትንቢት የተናገርኩት ነገር ሁሉ ልክ እንደተናገረው ሳይፈጸም ቀርቶ ያውቃልን? የጌታን ቃል አልነገርኳችሁምን? ይህንንም እጠይቃችኋለሁ፡ ወደ እናንተ መጥቼ ገንዘብ ለምኛችሁ አውቃለውን? ከእናንተ የወሰድኩት ነገር አለን? በቀጥታ የሰራዊት ጌታ እንዲህ ይላል ከሚለው ውጪ ያመጣሁት ነገር አለን? እግዚአብሔርም፡ ይህ እውነት መሆኑን፡ በእያንዳንዱ ጊዜ አረጋግጧል።” ያን ጊዜ ዝናብ እና ነጎድጓድ ላከባቸው (ጥቅሱን፡ እናንተ ራሳችሁ፡ በዚያ ታውቁታላችሁ።” ያም ሳሙኤል የእርሱ ቃል አቀባይ መሆኑን ለማረጋገጥ ነበረ።

105 ያን ጊዜ ሳሙኤል ፍጹም በሆነ መልኩ የእርሱ ተወካይ እንደነበረ፡ ዛሬ ደግሞ፡ መንፈሰ ቅዱሰ— መንፈሰ ቅዱሰ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ነው፥ መጽሐፍ ቅዱሰ የሚናገረውን በትክክል ይናገራል፥ መጽሐፍ ቅዱሰ የሚናገረውን ብቻ ያምናል፡ ከሱም በትንሹም ቢሆን፡ አይለይም።

106 እነርሱ ግን የተለየ ነገር ሊነግራቸው የሚችል ሰው ፈለጉ። ሕዝቡም የሳሙኤል ትንቢት ፍጹም እንዳልሆነ ሊናገሩ አልቻሉም። እነርሱም መልሰው እንዲህ አሉት፡ “ሳሙኤል ሆይ፡ በጌታ ሰም የተናገርከውን ሁሉ፡ ጌታ እንደተናገርከው እንዲሆን አድርጓል። አንድም ጉድለት የለም። ወደ እኛ መጥተህ ገንዘባችን አልለመንክም። ሳሰህን የቻልክ ነህ። ለአንተ ምንም አይነት ታላቅ፡ የተለየ ነገር እንድናደርግልህ ጠይቀህ አታውቅም። በአምላክህ ታምነሃል፡ እሱም ከሁሉም ነገር አድኖሃል። ቃላቶችህም እውነት ናቸው። በእግዚአብሔር ሰም የተናገርከው ነገር ሁሉ ተፈጽሟል። ይሁን እንጂ አሁንም ንጉሥ እንዲነግሥልን እንፈልጋለን።”

107 ባላንጣነትን አያችሁ? የዲያብሎሰ ተንኮል፡ በ—በሰዎች ላይ ሊ—ሊሠራ እንደሚችል ማየት ትችላላችሁ? ራሱን ወይም ራሷን ለመንፈሰ ቅዱሰ በማስገዛት፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በሚለው፡ ንጹሕ ሕይወት፡ ያልረከሰ ባሕርይ፡ የተለየ ሕይወት፡ የተለየ ወገን፡ ቅዱሰ ሕዝብ፡ እንግዳ-የሆነ ሕዝብ ከመሆን ይልቅ፥ ከዓለም ጋር የሚመሳሰሉ፡ እንደ ዓለም

የሚንቀሳቀሱ፡ እንደሚከተለው ወደሚሏቸው ቤተክርስቲያን የሚሄዱ ሕዝብ ሆኑ፡ “ምንም ችግር የለውም፡ ስራህን አድርግ ቀጥልበት።”

108 ምን እንደሆነ ይገባችኋል? እንዲህ ይላሉ፡ “ፈውስ ብሎ ነገር የለም። ኦህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለቤተክርስቲያን የማዕዘን ውበት ነበር።” በሌላ አነጋገር፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከቤተክርስቲያን አወጣና፡ ሰው አምጥቶ፡ የሃይማኖት ተቋም እንዲገነባ አደረገ ማለት ነው። በጭራሽ፡ በጭራሽ። እንደዚህ ያለ ነገር የለም። መንፈስ ቅዱስ፡ የእውነት ቃል፡ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ ይመራችኋል። አደራረጉ ግን—ያ ነው።

109 ሳኦል ወደ ሥልጣን መጣ። ታላቅም... ታላቅ ተከታዮችም አገኘ። ኦህ፡ የሚያማምሩ ጋሻዎች ነበሩት። ዘማሪዎች ነበሩት። ጋሻዎችና፡ ጦሮች ነበሩት። ኦህ፡ ሌሎቹን አሕዛብ ሁሉ በልጧቸዋል። ከማንም በላይ የሆነውን ማንም ሰምቶት የማያውቀውን ዲሞክራሲን አመጣላቸው።

110 በዛሬው ጊዜም የሃይማኖት ተቋማታችን እና አብያተ ክርስቲያናችን ያደረጉት ይህንኑ ነው። በዓለም ታላላቅ የተባሉ የቤተክርስቲያን ሕንጻዎች አሉን። በአለም ላይ በጣም የሚያማምሩ-አለባበስ የለበሱ ሰዎች አሉን። ሊመጡ የሚችሉ ከፍተኛ ስኮላርሺፕዎች አሉን።

111 ሳኦል ያንን ጦሩን መጠቀም የሚችሉትን ሰዎችን እንዳሰለጠናቸው፡ አገሮች እስኪፈሯቸው ድረስ ያንቀሳቀሱት ነበር። ሁሉም፡ የሰለጠኑ ሰዎች ነበሩ። አንድ ቀን፡ ግን፡ አንድ ተገዳዳሪ መጣ። የእስራኤልም ሠራዊት ሁሉ፡ በጫማቸው ውስጥ እስኪንቀጠቀጡ ድረስ ታላቅ ሆነባቸው። ጎልያድ “አምላካችሁ እንደምትሉት ከሆነ! እናንተም በደንብ የሰለጠናችሁ ከሆናችሁ፡” በማለት ተገዳደራቸው። እርሱም ተገዳደራቸው። ምን ማድረግ እንዳለባቸው አያውቁም። የነበሯቸው፡ ድንቃ ድንቅ ጋሻዎች፡ እርባና ቢስ ሆኑ። ጦሮቻቸው እርባና ቢስ ሆኑ። ከዚህ በፊት ሰምተውት የማያውቁት፡ አንድ ነገር፡ እየተከናወነ ነበር።

112 እናም በፍጹም አክብሮትና በአምላካዊ ትሕትና፡ በማክበር እና ክብር በሞላበት፡ በፍቅርና በክርስቲያናዊ ወንድማማችነት፡ ይህን እላለሁ፡ በቀደም ለት፡ በአፍሪካ ጋዜጣ ላይ፡ እንዳነበብኩት፡ ይህ የእኛ የቂስ ልጅ፡ የእኛ የሰብከተ ወንጌል ተገዳዳሪ፡ አንድ መሐመዳዊ፡ ቢሊ ግራሃምን እንደፈተነው እነብቤአለሁ። “አምላካችሁ አምላክ ከሆነ፡ አደርጋለሁ ብሎ እንደተናገረ የታመሙትን አሁን ይፈውስ፡” አለው። የቂስም ልጅ፡ ከሠራዊቱ ሁሉ ጋር፡ አፋቸውን ዘጉና፡ ተሸንፈው አገሩን ለቀው ወጡ። ይህ ውርደት ነው። አምላካችን ግን አምላክ ነው።

113 ጥሩ አብያተ ክርስቲያናት አሉን። ጥሩ የወንጌል ሰባኪነት አለን። የሚከፈልላቸው ዘማሪዎች አሉን። ምርጥ የመዘምራን ቡድኖች አሉን፡ በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ካቴድራሎች አሉን። በጣም ጥሩ የሆኑ ሰዎች አሉን፡ በጣም ብዙ ገንዘብ አለን። ምሁራን አሉን። ሥነመለኮት እስከ ጥግ ድረስ አለን፡ መስበክ እንችላለን፡ መናገር እንችላለን። ወንጌልን መስበክ እና ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣት፡ በየዓመቱም በሚሊዮኖች የሚቈጠሩ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያን ማምጣት እንችላለን። [ካቴፑ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።] እንዲህ ዓይነቱን ተግዳሮት እንዴት መቋቋም እንደሚቻል የማያውቁ፡ ቅጥረኛ ዘማሪዎች፡

ምሁራዊ ወንገላዊነት አሉን። ስለሱ ምንም አያውቁም። ስለ መፈወስ ኃይሉ ኃይሉ፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ በካንሰር እየተሰቃየ ከሚሞት ሰው የሞትን ጥላ ስለሚያነሣው፡ እና ነጻ ስለሚያወጣ ኃይሉ እውቀት የላቸውም። ምንም አያውቁም። ሳኦልና ሰው-ሠራሽ ቡድኖቹ እንዳደረጉት፡ በዚያ መሰክ አልሠለጠኑም።

114 ነገር ግን ለእግዚአብሔር ህዝብና፡ ለእናንተም ለልጆቹ እንዲህ እላችኋለሁ፡ ይህም እግዚአብሔር ያለ ምስክርነት እንደማይተዋችሁ እንድታውቁ ነው።

115 ሳኦል፡ ሳኦል ስለዚህ ጉዳይ፡ ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ግን በጎቹን የቤተ ክርስቲያን እንክርዳድ የማይመግብ ሰው ዳዊትን፡ በኮረብቶቹ ጀርባ ጠብቆ አስቆይቶት ነበር። እርሱም ወደ እረፍት ውሃ እና ወደ አረንጓዴ መስክ ይመራቸው ነበር። የአባቱን በጐች ጠባቂ ነበር። የአባቱን በግ ለመውሰድ የሆነ ነገር ሮጦ ቢገባ፡ ጠላት ቢመጣ፡ ያንን በግ የሚያድን፡ የእግዚአብሔርን ኃይል ያውቃል።

116 እግዚአብሔር አሁንም፡ በእግዚአብሔር ኃይል፡ የእግዚአብሔርን በግ ለማዳን ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቀውን፡ ዳዊትን በአንድ ሰፍራ አለው። እስከ አሁን ድረስ የሚያውቀው ይህ ብቻ ነው።

117 እምነት ነበረው። ስለ ሳኦል ትጥቆች የሚያውቀው ነገር አልነበረም፡ እነዚያም አልሰፈለጉትም። የሃይማኖት ተቋማቸውን አልፈለገም። አሮገውን የጦር ትጥቅ መያዝ አልፈለገም። “እኔ ስለዚህ ጉዳይ ምንም አላውቅም፡ ነገር ግን የማውቀውን ኃይል በመጠቀም ሊሂድ፡” አለ። የአባቱን በጐች ይመግብ ነበር። መሰኩን እየተንከባከበ ነበር። ትክክለኛውን አይነት ምግብ ያበላቸዋል፡ እነሱም በሕይወት ይኖሩ ያድጉም ነበር።

118 “ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም። ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።” እውነተኛው እረኛ ይመግባቸዋል። “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ነው።” ጠላት በህመም፡ አንድን ሰው ቢይዝ፡ የእግዚአብሔርን ኃይል ያውቃል።

119 በዚያ ቆሞ የነበረውን፡ ትንሹ ዳዊትን እዩት። እንዲህ አለው፡ “ሰውዬ ከታናሽነቱ ጀምሮ፡ ተዋጊ ነው። ከወጣትነቱ ጀምሮ፡ ከጦር መሣሪያና ከጦር ትጥቅ በቀር የሚያውቀው ነገር የለም። በደንብ የሰለጠነ ነው። እሱ የሃይማኖት ምሁር ነው። እና ስለእነዚህ ነገሮች ዕውቀት የለህም።”

120 እሱም፡ “እውነት ነው፡ ጌታዬ። ስለ ሃይማኖታዊ ስልጠናው ምንም የማውቀው ነገር የለም። አንድ ነገር ግን አውቃለሁ፡ ይህም፡ የአባቴን በግ ለመንጠቅ፡ ጠላት በመጣ ጊዜ፡ በእግዚአብሔር ኃይል እሄድ ነበር። እኔም አድናቸው ነበር። በደኅናም ወደ ጤንነቱ እመልሳቸው ነበር። ወደ ለመለመው መስክና እረፍት ወዳለው ውኃ መልሼ አመጣቸው ነበር። ከ—ከጠቦቶቼ መካከል አንዱን በወሰደ ጊዜ፡ እንድቆራርጠው አንበሣውን ድብንም፡ በእጄ አሳልፎ የሰጠኝ ይህ አምላክ፡ አሁንም ይህን ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ለመግደል አብሮኝ ይሄዳል።”

የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያስፈልገናል። እኔ ቀኖቼን አላውቅም፥ ማንም አያውቅ።

121 በቀደም ማለዳ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ነበር። እና… ተኝቼ ሳለሁ፡ ዮሴፍም ታምሞ በሕልም አየሁት፡ እናም እንድጸልይለት አነሳሁት። ከእንቅልፌ ስነቃ፡ በጣም ተበሳጨሁ። “እንዴ፡ ምናልባት ጆሴፍ ሊታመም ይሆናል፡” አልኩኝ።

122 እነሆም አየሁ፡ ትንሽ፡ ጥቁር ጥላ፡ ወይም በቡናማ ቀለም ያለው፡ ከፊቴ የሚሄድ ነገር ነበር። እነሆም እኔን ይመስላል። እና አየሁት። እና ከኋላዬ የሚመጣው አንድ ነጭ ነበር፡ እርሱ ነበር። ባለቤቴ ከእንቅልፏ ነቅታ እንደሆነና፡ ራእዩን ማየት ትችል እንደሆነ ለማየት ወደሷ፡ ተመለከትኩ። ነገር ግን ተኝታ ነበር።

123 እኔም፡ “ኦህ፡ ጌታ ሆይ፡ ይቅርታ አድርግልኝ። ነገር ግን፡ ያ ሕይወቴ ነበር። ያደረግኩትን ሁሉ እንድፈጽም ያነሳሳኸኝ አንተ ነበርክ። የሆነ ነገር በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ፡ እኔ ይህን የምታደርገው አንተ ነህ ብዬ እሰባለው። እናም ሰይጣን ከእሱ ሊያርቀኝ እየሞከረ እንደነበር ተገነዘብኩ” አልኩኝ። እኔም እንዲህ አልኩ፡ “አንተ ብቻ ልትመራኝ ከቻልክ።” እኔም ስመለከት፡ በሰው ላይ አይቼው የማላውቀውን በጣም ቄንጆ ፊት አየሁ። እሱ ከፊት ለፊቴ ነበር፡ ወደ ኋላ እያየኝ። እጁን አነሣና እጄን ያዘኝና፡ **በዚህ** መንገድ መንቀሳቀስ ጀመረ። ራእዩ ጥሎኝ ሄደ። ባለፈው እሁድ ጠዋት፡ እኔም ፡ በጠዋት ከእንቅልፌ ነቅቼ ነበር። ይህን ራዕይ ያ… ያየሁት፡ ቅዳሜ ዕለት ነው።

124 ሁሌም እጨነቅ ነበር፡ ሁሌም ስለመሞት እሰብ ነበር። የእኔ፡ አምሳ መሙላት፡ ጊዜዬ፡ እንዲህ አይደለም… በጣም ረጅም ነው ብዬ አላሰብም። እናም በዚያ ቲዮፈኒ፡ ሰማያዊ አካል ውስጥ ምን እሆናለሁ ብዬ እሰባለሁ። “ውድ ጓደኞቼን አያቸው ይሆን፡ እላለሁን፡ ነጭ ጉም ሲያልፍ፡ እንዲህ እላለሁን፡ ‘ወንድም ኔቪል እያለፈ ነው’ ወይስ፡ “እንዴት ነህ፡ ወንድም ብራንሃም’ ማለት አይችልም ይሆንን? ያን ጊዜ ኢየሱስ ሲመጣ፡ እንደገና ሰው እሆናለው።” እያልኩ ብዙ ጊዜ እሰበዋለሁ።

125 በሕልሜ ወደ ምዕራብ አካባቢ ሆኜ አየሁ። እና በአንድ ቅጠላማ አካባቢ እየወረድኩ፡ ሚስቴ ከእኔ ጋር ነበረች፡ እና በሜንጦ እሳ እያጠመድን ነበርን። ቆም ብዬ—በሩን ከፈትኩት። ሰማዩም በጣም ቄንጆ ነበር። እዚህ እንዳሉት አይነት ሸለቆዎች አይመስሉም። ሰማያዊ እና፡ የሚያምር ነጭ ደመናዎች ነበሩ። ለባለቤቴም፡ “የኔ ማር፡ ከብዙ ጊዜ በፊት፡ እዚህ መኖር ነበረብን፡” አልኳት። እሷም “ቢሊ፡ ለልጆቹ ሲባል፡ እንዲህ ማድረግ ነበረብን።” እኔም “ያ ነው… ” አልኳትና፡ ያን ጊዜ ከእንቅልፌ ነቃሁ።

126 “በጣም እያለምኩ ነው! ለምን ይሆን፡” ብዬ እሰብኩ። ወደ ታች ተመለከትኩና፡ እሷም አጠገቤ ተኝታ ነበር።

127 እኔም ብዙዎቻችሁ እንደምታደርጉት፡ በትራሴ ላይ ቀና ብዬ፡ ራሴን በአልጋው ራስ ላይ አ—አድርጌ፡ እጆቼን ከኋላዬ አደረኩ። በዚያም **እንዲህ** ተኛቼ ነበር። አልኩም፡ “እቤት፡ ላይኛው ህይወት፡ ምን ይመሰል ይሆን ብዬ እሰብኩ። ገና ምንም ሳላደርግ፡ ሃምሳ አመት ሞላኝ። ሟች እንደማልሆን እውቃለሁና፡ ጌታን ለማገዝ አንድ ነገር ማድረግ በቻልኩ። ግማሽ ዕድሜዬ አልፏል፡ ቢያንስ፡ ወይም ከግማሽ በላይ። እንደ ህዝቤ ዕድሜ ብቆይም እንኳ፡ አሁንም ግን ግማሹ ድሜዬ አልፏል።” እና ዙሪያውን ተመለከትኩ። እና እዚያ ተኛቼ ነበር፡ ለመነሳት ተዘጋጅቼ ነበር። ሰባት ሰዓት ገደማ ነበር። እኔም “ዛሬ

ጠዋት፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ ብዬ አሰባለሁ። ድምጼ ከተያዘ፡ ወንድም ኔቪል ሲሰብክ መስማት እፈልጋለሁ፡” አልኩ።

128 ስለዚህም “ማር፡ ነቅተሻል? ” አልኳት፡ እሷም በጥልቀት ተኝታ ነበር።

129 እና ይህ እንዲያመልጣችሁ አልፈልግም። ይህ ነገር እኔንም ቀይሮኛል። ከእንግዲህ የመጀመሪያውን ብራንሃም መሆን አልችልም።

130 እናም ተመለከትኩኝ። የሆነ ነገር ሲናገር ሰማሁ፡ “ገና መጀመሪያህ ነው፡ ውጊያውን ቀጥል። ዝም ብለህ ቀጥል።”

131 ለአንድ ደቂቃ ጭንቅላቴን ነቀነቅኩ። “አይ፡ ምናልባት እንዲህ እያሰብኩ ሊሆን ይችላል፡” ብዬ አሰብኩ። አንዳንዶች ሰዎች ምናቦች ሊኖራቸው እንደሚችል ታውቃላችሁ። እኔም “ይህን በምናቤ ብቻ አሰቤው ሊሆን ይችላል፡” አልኩ።

እንዲህ ይላል፡ “ውጊያውን ቀጥል። ጉዞህን ቀጥል። ጉዞህን ቀጥል።”

132 እኔም፡ “ምናልባት እኔ ብዬው ይሆናል።” አልኩና ከንፈሮቼን በጥርሶቼ መካከል አድርጌ፡ እጄን በአፌ ላይ አደረኩ።

133 ድምጹም እንደገና መጣ፡ አለኝም፡ “በመንገዱ መጨረሻ ላይ ምን እንዳለ ብቻ ብታውቅ ኖር! ብቻ ጉዞህን ቀጥል!”

134 እናም ግራሃም ስኔሊንግ፡ ወይም ሌላ ሰው፡ ያንን መዝሙር እንዲህ ሲል ሲዘምር የሰማሁ መሰለኝ (እዚህ የሚዘመር ነው፡ እነ እና ማኢ እና ሁላችሁም እዚህ ትዘምሩታላችሁ።)፦

በናፍቆት እጅግ ታምሜአለሁ፡ ኢየሱስን ማየት ፈልጌአለሁ፡
ጣፋጭ የወደብ ደወሎች ድምጾች መስማት ናፍቆኛል፥
መንገዴን ያበራል ፍርሃቴም ያጠፋል፥
ጌታ ሆይ፡ ከጊዜው ባሻገር እንዳይ ፍቀድልኝ።

እዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲዘመር ሰምታችኋል።

135 የሆነ ነገር “ከአድማስ ባሻገር ያለውን ማየት ትፈልጋለህ፡” ሲለኝ ሰማሁ?

“ያ በጣም ይረዳኛል፡” አልኩት።

136 እነሆም አየሁ። በቅጽበት ውስጥ፡ በ... በቀረችኝ ትንፋሽ ወደ ሚያንሸራትት ስፍራ ደረስኩ። ወደ ኋላዬ ሳይ፡ አልጋው ላይ፡ ተኝቼ ነበር። “ይህ በጣም እንግዳ ነገር ነው፡” አልኩ።

137 አሁን፡ ይህ ነገር በእናንተ እንዲደገም አልፈልግም። ይህ የሆነው ከቤተክርስቲያኔ በፊት፡ ወይም ለበጎቼ ፓስተር ከመሆኔ በፊት ነው። ያም ሆነ ይህ፡ በዚህ አካል ውስጥ ወይም ከዚህ አካል ውጪ፡ ወይሰ ንጥቀት ይሆን አላውቅም፡ ከዚህ በፊት እንዳየሁት አይነት ራዕይ አልነበረም። እዚያም ማየት እችል ነበር፡ እዚህም ማየት እችል ነበር።

138 ወደዚያ ስፍራ በደረስኩ ጊዜ፡ ከዛ በፊት እንዲህ ብዛት ያላቸው ሰዎች እየሮጡ፡ እየጮሁ “ኡህ፡ ውድ ወንድማችን!” ሲሉኝ አይቼ አላውቅም፡

139 እኔም ተመለከትኩ። እና ወጣት ሴቶች፡ ምናልባት በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ፡ ከ18 እስከ 20 እድሜ ያሉ፡ “ውድ ወንድማችን!” እያሉ ክንዶቻቸውን እየዘረጉ፡ ሰያቅፉኝ እና ሲጮሁ ነበር፡

140 እነሆ ወጣቶች፡ በወጣትነታቸው ብሩህነት ይመጣሉ። ዓይኖቻቸውም የሚያንጸባርቅ እና በጨለማ ላይ እንደሚያበሩ ከዋክብት ነበር። ጥርሶቻቸውም እንደ ዕንቊ ነጭ ነበሩ። እነሱም እየጮኹ፡ እየያዙኝ፡ እየጮኹ፡ “ኦህ፡ ውድ ወንድማችን!”

141 እኔም ቆምኩኝ፡ እና ተመለከትኩኝ። እኔም ወጣት ነበርኩ። እጆቼን ከጭንቅላቴ ጀርባ አድርጌ፡ አሮጌውን አካሌን ተኝቶ አየሁት። እኔም “ይህን አልተረዳሁትም፡” አልኩ።

142 እና እነዚህ ወጣት ሴቶች ክንዶቻቸውን እየዘረጉ ያቅፉኝ ነበር። አሁን፡ ይህ ድብልቅ ጉባኤ መሆኑን እገነዘባለሁ፡ ይህንም የምለው በመልካም እና በተሰበረ መንፈስ ነው። ወንዶች ያለ ሰው ሰሜት እጃቸውን በሴቶች ላይ መጫን አይችሉም፡ ነገር ግን እዚያ ያ የለም። ትናንትም ሆነ ነገ የለም። ደክሟቸው አያውቅም። እነርሱ... በሕይወቴ እንደዛ ዓይነት ቈንጆ ሴቶች አይቼ አላውቅም። ፀጉራቸው እስከ ወገብ ድረስ ረዥም፡ ቀሚሳቸው እስከ እግራቸው ድረስ ነበር። ብቻ ያቅፉኛል። እዚያ የተቀመጠችው፡ የራሴ እኅት እንኳ፡ እንደምታቅፈኝ ዓይነት እቅፍ አልነበረም። እየሳሙኝ አልነበረም፡ እኔም እየሳምኳቸው አልነበረም። የሆነ ዓይነት—ነገር ነው ምንም ለማለት ቃል አ—አጣው፡ በቃላት መግለጽ አልችልም። “ፍጹም” ብለው አይገልጸውም። “ምርጥ” ብለው እንኳን አይተካከለውም፡ በጭራሽ። በፍጹም የማልገልጸው ነገር ነበር... ይህን ለመረዳት እዚያ ብቻ መሆን አለባችሁ።

143 **ወደዚህም፡ ወደዚያም** ተመለከትኩ። በሺዎች የሚቈጠሩ፡ እየመጡ ነበር። እኔም “ይህን አልገባኝም፡” አልኩ። እንዲህ አልኩ፡ “መልካም፡ እነርሱ... ”

144 እነሆም ሆፕ ደግሞ መጣች። እሷ የመጀመሪያ ሚስቴ ነበረች። ሮጠች፡ በጭራሽ “ባሌ፡” ብላ አልጠራችኝም። “ውድ ወንድሜ፡” አለችኝና፡ እሷ ሰታቅፈኝ፡ ሌላ ሴት ቆማ ነበር፡ እሷም አቅፋኝ ነበር፡ ከዚያም ሆፕ ያችን ሴት አቀፈቻት፡ እና እርስ በርስ ተቃቀፉ። እንዲህ አሰብኩ፡ “ኦህ፡ ይህ የተለየ ነገር መሆን አለበት። ሊሆን አይችልም... የሆነ ነገር'ማ አለ... ” እንዲህ አሰብኩ፡ “ኦህ፡ ወደዚያ ወደ አረጀው ሬሳ ዳግመኛ መመለስ እፈልግ ይሆንን? ”

145 ዙሪያዬን ተመለከትኩና። እንዲህ አሰብኩ፡ “ይህ ምንድን ነው? ” እኔም በጥሩ ሁኔታ፡ ተመለከትኩና። “ይህን ልረዳው አልችልም፡” አልኩ። ሆፕ ግን፡ ኦህ፡ የክብር እንግዳ መሰላ ነበር። የክብር እንግዳ እንጂ፡ ሌላ አትመስልም ነበር።

146 እናም አንድ ድምፅ ከክፍሉ ውሰጥ ተናገረኝ፡ እንዲህ ሲል ሰማሁ፡ “ይህ አንተ የሰበክከው መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ ፍጹም ፍቅር ነው። ያለ እሱ ምንም ነገር እዚህ ሊገባ አይችልም።”

147 ወደዚያ ለመግባት፡ ፍጹም ፍቅርን እንደሚጠይቅ፡ በሕይወቴ ውሰጥ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ፡ የበለጠ አረጋገጥኩ። መቅናት የለም። ድካምም አልነበረም። ሞትም አልነበረም። በሽታም በጭራሽ፡ እዚያ ሊኖር አይችልም።

ሟችነት፡ ሊያስረጅ የሚችል—ነገር የለም። እነሱ… ሊያለቅሱ አይችሉም። ደስታ ብቻ ነበር።

148 “ኦህ፡ ውድ ወንድሜ!” እነሱም ወደ ላይ ወሰዱኝና፡ አንድ ትልቅ ከፍታ ቦታ ላይ እኔን አስቀመጡኝ።

149 “በህልም ላይ አይደለሁም። ስ—ሰውነቴ እዚህ አልጋው ላይ ተኝቶ ወደ ኋላ እየተመለከትኩ ነው፡” ብዬ አሰብኩ።

150 እዚያም አስቀመጡኝ። እኔም፡ “ኦህ፡ እዚህ ላይ መቀመጥ የለብኝም” አልኳቸው።

151 ከሁለት አቅጣጫ፡ ሴቶችና ወንዶች፡ ገና በለጋ ወጣት ዕድሜአቸው፡ እየጮኹ ይመጣሉ። እንዲትም ሴት እዚያ ቆማ ነበር፡ እና እንዲህ ብላ ጮኸች፡ “ኦህ፡ ውድ ወንድሜ! ኦህ፡ አንተን እዚህ በማየታችን በጣም ደስ ብሎናል።”

እኔም “ይህ አልገባኝም፡” አልኩ።

152 ያን ጊዜም ከላይ፡ ይናገረኝ የነበረው ድምጽ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ታውቃለህ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነቢያት ወደ ወገኖቻቸው ይከማቹ እንደነበረ ተጽፏል።”

እኔም “አዎ፡ በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ ያንን ጥቅስ አስታውሳለሁ፡” አልኩት።

እንዲህም አለኝ “መልካም፡ ከወገኖችህ ጋር መከማቸት ማለት ይህ ነው፡” አለኝ።

እኔም “እንግዲያውስ የምር ይሆናሉ፡ እኔም ልዳሰሳቸው ይቻለኛል፡” አልኩት።

“ኦህ፡ አዎን።”

153 “ነገር ግን፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ናቸው። ቢሆንም ብዙ ብራንሀሞች የሉም፡” አልኩት።

154 ያ ድምፅም፡ “እነዚህ ብራንሀሞች አይደሉም። እነዚህ አንተ የቀየርካቸው ናቸው። ወደ ጌታ ያመጣሃቸው ሰዎች ናቸው።” እንዲህም አለ፡ “በጣም ቆንጆዎች ናቸው ብለህ የምታስባቸው፡ ከመካከላቸው ያሉ አንዳንድ ሴቶች፡ ወደ ጌታ ስትመራቸው ከዘጠና ዓመት በላይ ዕድሜ የነበራቸው ናቸው። ‘የእኛ ውድ ወንድማችን!’” እያሉ መጮሃቸው አያስደንቅም፡

155 እና በአንድነትም፡ ሁሉም፡ እንዲህም አሉ፡ “አንተ ባትሄድ ኑሮ፡ እኛ እዚህ ባልተገኘን ነበር።”

ዙሪያውን ተመለከትኩ። “መልካም፡ ምንም አልገባኝም፡” ብዬ አሰብኩ።

“ኢየሱስ የት አለ? እኔ እሱን ማየት፡ እጅግ በጣም እፈልጋለሁ፡” አልኩ።

156 እነርሱም “አሁን፡ እሱ ትንሽ ከፍ ብሏል፡ **በዚያ** አቅጣጫ፡” አሉኝ። “አንድ ቀን እሱ ወደ አንተ ይመጣል፡” አሉኝ። አያችሁ? አሉኝም፡ “የተላክኸው፡ መሪ ለመሆን ነው። እግዚአብሔርም ይመጣል። እርሱ ሲመጣ፡ ከሁሉ በፊት ባስተማርካቸው ትምህርት መሰረት ይፈረድብሃል፡ እነርሱ፡ ቢገቡም ባይገቡም ይፈረዳል። እኛም የምንገባው በአንተ አስተምህሮ መሰረት ነው።”

157 “ኦህ፡ በጣም ደስ ይለኛል። ጳውሎስ፡ እርሱም እንደኔ እዚህ ይቆማልን? ጴጥሮስስ እንደዚህ ይቆማልን? ”

“አዎን።”

158 እኔም እንዲህ አልኳቸው፡ “እንግዲያውስ እነርሱ የሰበኩትን ቃል ሁሉ ሰብኬአለሁ። በፍጹም ከዚህ አልወጣሁም፡ ወደ ግራ ወደ ቀኝም አላልኩም። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቁ፡ እኔም እንዲሁ። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንዳስተማሩ፡ እኔም አስተማርሁ። እነርሱ ያስተማሩት ሁሉ፡ እኔም አስተማርሁ።”

159 ህዝቡም ጮኹና፡ እንዲህ አሉ፡ “ያንን እናውቃለን። አንድ ቀን ከአንተ ጋር፡ ተመልሰን ወደ ምድር፡ እንደምንሄድ እናውቃለን።” እንዲህ አሉ፡ “ኢየሱስ ይመጣል፡ እንደ ሰበክከው ቃል ይፈረድብሃል። በዚያን ጊዜ ተቀባይነት ካገኘህ፡ ደግሞም ተቀባይነትን ታገኛለህና፡” እንዲህም አሉ፡ “ከዚያም እኛን እንደ አገልግሎትህ ሽልማት አድርገህ፡ በፊቱ ታቀርበናለህ።” “አንተ ወደ እርሱ ትመራናለህ፡ ሁላችንም፡ ለዘላለም ለመኖር፡ ወደ ምድር እንመለሳለን፡” አሉኝ።

“አሁን መመለስ አለብኝን? ” አልኳቸው፡

“አዎን። ጉዞህን ግን ቀጥል።”

160 አየሁ። ማየት በምችለው ልክ፡ ህዝቡን አይቻለሁ፡ አሁንም፡ “ውድ ወንድማችን!” እያሉ እየጮኹ፡ ሊያቅፉኝ ይፈልጉ ነበር፡

161 በዚያን ጊዜ አንድ ድምፅ እንዲህ አለ፡ “እስከ ዛሬ የወደድካቸው፡ አንተንም የወደዱህም ሁሉ፡ እግዚአብሔር እዚህ ለአንተ ሰጥቶሃል።” እኔም ተመለከትኩ። እነሆ የድሮ ውሻዬ መጣ፡ እየተራመደ መጣ። እንሆ ፈረሴም መጣ፡ ትከሻዬ ላይ ራሱን አኖረና፡ የፍቅር ድምጹን አወጣ። አለኝም፡ “በሕይወትህ የወደድካቸው በሙሉ፡ እና የወደዱህን ሁሉ፡ እግዚአብሔር በአገልግሎትህ፡ እማካኝነት በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል።”

እኔም ከዚያ ውብ ስፍራ ስንቀሳቀስ ተሰማኝ።

162 ዙሪያየን ተመለከትኩ። “ማር፡ ነቅተሻል? ” አልኳት፡ አሁንም ተኝታ ነበር።

163 እኔም፡ “አምላክ ሆይ! አቤቱ፡ እርዳኝ፡ አምላክ ሆይ። በአንዲት ቃል አመቻምች ዘንድ ፈጽመህ አትፍቀድልኝ። ከቃሉ ጋር በእውነት እንድወግን፡ እና እንድሰብክ አድርገኝ። የሚመጣውም የሚሄደውም፡ ማንም ሰው ምንም ቢያደርግ ምንም ግድ አይሰጠኝም፥ ምንም ያህል ሳኡሎች... የኪሽ ልጆች ብዙ **ይህ፡ ያ**፡ ወይም **ሌላ** ቢነሱም ግድ አይሰጠኝም። ጌታ ሆይ፡ ወደዚያ ቦታ እንድደርስ ፍቀድልኝ” ብዬ አሰብኩ። የሞት ፍርሃት ሁሉ...

164 ይህንን የምለው፡ ዛሬ ጠዋት፡ መጽሐፍ ቅዱስ ፊት ለፊቴ አድርጌ እናገራለሁ። ማሳደግ ያለብኝ፡ የአራት አመት፡ ምስኪን ልጅ አለኝ። የዘጠኝ-ዓመት-ልጅ አለችኝ፥ ገና ታዳጊ ናት፡ የጌታን መንገድ በመከተላቸው፡ ምስጋናዬ ብዙ ነው። አምላኬ ሆይ፡ ልጆቼን በአምላክ ቃል አስተምሬ አሳድጋቸው ዘንድ፡ እንድኖር ፍቀድልኝ።

165 ከዚያ በላይ ደግሞ፡ ዘጠና-ዓመት-ሴቶች እና ወንዶች፡ ሁሉም ዓይነት ሰዎች፡ መላው ዓለም ወደ እኔ የሚጮሁ ይመስላል፡ “አንተ ባትሄድ ኖሮ፡ እዚህ ባልተገኘን ነበር።”

166 እናም፡ አምላክ ሆይ፡ በውጊያው እንድጸና እርዳኝ። ሞት ከመጣብኝ ግን፡ አልጨነቅም። ከውርደት እና ከመበሰበስ፡ ወደዚህ ማለፌ፡ ደስታና፡ ሐሴት ይሆንልኛልና።

167 አንድ መቶ ቢልየን ማይሎች፡ ሰኮር ብሎክ፡ ወደ ላይ ርቄ መውጣት፡ ከቻልኩ፡ ያ ፍጹም ፍቅር ነው፡ አሁን ወዳለንበት እስክንደርስ ድረስ፡ እያንዳንዱ እርምጃ ወደዚህ፡ እየጠበበ ይሄዳል። የጥፋት ጥላ ብቻ ነው የሚሆነው፡ በሆነ ስፍራ ላይ የሆነ ነገር እንዳለ የምንገነዘበውና የሚሰማን ትንሽ ነገር ብቻ ነው። ምን እንደሆነ አናውቅም።

168 የተወደዳችሁ፡ ውድ፡ ወዳጆቼ ሆይ፡ የወንጌል ወዳጆቼ፡ ለእግዚአብሔር የተወለዳችሁ ልጆቼ፡ እኔን ፓስተራችሁን፡ ስሙኝ። ይህን ላስረዳችሁ፡ የምችልበት መንገድ ቢኖር ደስ ባለኝ ነበር። ቃላቶች የሉም፥ ማግኘት አልቻልኩም፥ የትም አይገኝም። ብቻ ከዚህች ከመጨረሻዋ ትንፋሽ በላይ፡ በፊት ካያችሁት ከሁሉ የላቀ ነገር አለ… ለማብራራት ምንም መንገድ የለም። ምንም መንገድ የለም። ብቻ ይህን ማብራራት አልችልም። ነገር ግን ምንም አድርጉ ምን፡ ጓደኞቼ፡ ፍጹም ፍቅር እስክታገኙ ድረስ ሁሉንም ነገር ወደ ጎን አስቀምጡት። ሰው ሁሉ፡ ጠላታችሁም፡ ነገር ሁሉም መውደድ ወደምትችሉበት አቅም ድረሱ።

169 እዚያ ያደረኩት አንድ ጉብኝት፡ ለእኔ፡ እኔን የተለየ ሰው አድርጎኛል። ከእንግዲህ፡ በፍጹም፡ በጭራሽ የመጀመሪያውን ተመሳሳይ ወንድም ብራንሃም መሆን አልችልም። አውሮፕላኖቹ ቢንገጫገጩ፡ መብረቅ ቢበራ፡ ሰላዩ ጠመንጃ ቢደቅንብኝ፡ ምንም ይሁን ምን፡ ለውጥ አያመጣም። በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ውጊያውን እቀጥላለሁ። እኔ የምችለውን ያህል ለሁሉም ፍጡር እና ሰው ሁሉ፡ ወንጌልን ሰብኬአለሁና፡ ወደዚያች ሩቅ ውብ ምድር አሳመንኳቸው።

170 ከባድ ሊመስል ይችላል። ብዙ ጥንካሬ ሊጠይቅ ይችላል። ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ አላውቅም። በሰጋ ሰንናገር፡ አናውቀውም። በ… በቀደም በምርመራዬ ላይ፡ “ሃያ-አምስት ዓመት ከባድ እና፡ ጥሩ ሕይወት አለህ። ጠንካራ ነህ፡” አለኝ። ያ ረድቶኛል። ይሁን እንጂ፡ ኦህ፡ ያ አይደለም። እሱ አይደለም። **እዚህ** ውስጥ የሆነ ነገር አለ። ይህ የሚበላሸው የማይበላሸውን መልበስ አለበት። ሟቹም የማይሞተውን መልበስ አለበት።

171 የቂስ ልጆች ሊነሱ ይችላሉ። እኔ… የሚያደርጉት መልካም ነገር ሁሉ፡ ለድሆችና ለበጎ አድራጎት ስለመስጠታቸው፡ ምንም መጥፎ ተቃውሞ የለኝም። ሳሙኤልም ሳኦልን፡ ለምን፡ “አንተም ደግሞ ትንቢት ትናገራለህ፡” ብሎት እንደነበር አስታውሱ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል ብዙዎቹ ታላላቅና፡ ኃያላን ሰባኪዎች ናቸው፡ ቃሉን እንደ ሊቀ መላእክት ሊሰብኩት ይችላሉ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን እሱ አይደለም። እግዚአብሔር ንጉሣቸው መሆን ነበረበት። ወንድም፡ እኅቶች፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲመራችሁ ፍቀዱለት።

እስቲ ለፍታ ያህል ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

> በናፍቆት እጅግ ታምሜአለሁ፡ ኢየሱስን ማየት
> ፈልጌአለሁ፡
> ጣፋጭ የወደብ ደወሎች ድምጾች መስማት ናፍቆኛል፥
> መንገዴን ያበራል ፍርሃቴም ያጠፋል፥

ጌታ ሆይ፡ ከጊዜው ባሻገር እንዳይ ፍቀድልኝ።
ጌታ ሆይ፡ ከኀዘንና ከፍርሃት መጋረጃ ባሻገር እንዳይ ፍቀድልኝ፡
ያንን ብሩህ አየር እንድመለከት ፍቀድልኝ፥
እምነታችንን ያጠናክራል ፍርሃትን ሁሉ ያሰወግዳል፥
ጌታ ሆይ፡ ከጊዜው ባሻገር እንዳይ ፍቀድልኝ።

172 ጌታ ሆይ፡ ይህች ትንሽ ቤተ ክርስቲያን፡ ዛሬ ጠዋት፡ ብቻ ከአድማስ ማዶ መመልከት ብትችል፡ በካከላቸው፡ ከፍጹምነት በቀር፡ ምንም አይነት መከራ፥ በሽታም ቢሆን፥ ፈጽሞ እንደማይሆንባቸው እርግጠኛ ነኝ። በዚህ እና በዚያ መካከልም፡ ከእርጅና እስከ ወጣትነት፡ ከጊዜ እስከ ዘለአለማዊነት፡ ከነገ ድካም፡ እና ከትላንት ሃዘን፡ እስከ ዛሬው የዘላለም ዘመን ፍፁምነት ድረስ እንዲት ትንፋሽ ብቻ አለች።

173 ጌታ ሆይ፡ በዚያ የፍቅር መንገድ የማያውቅህ ሰው፡ እዚህ ካለ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ሰዎች ሁሉ፡ እንድትባርክ እጸልያለሁ። እና በእውነት፡ አባት ሆይ፡ ያ ዓይነት ፍቅር፡ አዲስ ልደት፡ ዳግመኛ መወለድ የሌለው ማንም ቢሆን ወደዚያ ቅዱስ ሰፍራ መግባት አይችልም። መንፈስ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡ ፍቅር ነው፡ እኛም ይህ እውነት እንደሆነ እናውቃለን። ምንም እንኳን በእምነታችን ተራራዎችን ብናንቀሳቅሰም፡ ታላላቅ ነገሮችን ብናከናውንም፡ አሁንም፡ ያለዚያ ፍቅር ግን፡ በዚያ ታላቅ መሰላል በጭራሽ ልንወጣ አንችልም። ፍቅር ግን፡ ከምድራዊ ምኞት በላይ ከፍ ከፍ ያደርገናል። አባት ሆይ፡ እዚህ ያሉትን ሰዎች እንድትባርክ፡ እጸልያለሁ።

174 እናም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ያ፡ የሰማኝ ሰው ሁሉ፡ ይህንን እውነት ይመሰክር፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ እንደ ጥንቱ፡ እንደ ሳሙኤል ምስክር ትሆንልኝ ዘንድ፡ "በሰምህ ከእውነት በቀር ሌላ ነገር ተናግሬአለሁን? " እነርሱ ዳኞች ናቸው። እናም ጌታ ሆይ፡ ወደዚያች ምድር ያመጣኸኝ አንተ እንደሆንክ፡ አሁን እነግራቸዋለሁ። ያም እውነት እንደሆነ አንተ ታውቃለህ።

175 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ አንተን የማያውቁ ካሉ፡ ይህች ሰዓት፡ "ጌታ ሆይ፡ ፍቃድህን በውስጤ አድርግ" የሚሉባት ሰዓት ትሁን። ይሁን በል፡ አባት ሆይ።

176 እናም አሁን፡ ራሳችሁን፡ ዝቅ እንዳደረጋችሁ፡ እጆቻችሁን፡ ከፍ አድርጋችሁ እንዲህ በሉ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ለእኔ ጸልይ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ በውስጤ ይሁን።"

177 አሁን በያላችሁበት ሆናችሁ፡ በጣም ጣፋጭ በሆነ መንገድ፡ ለምን አባታችሁን፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ በልቤ ውስጥ፡ ዛሬ፡ የዓለምን ነገሮች ሁሉ እጥላለሁ። በሕይወቴ ሁሉ፡ አንተን ለመውደድና ለማገልገል፡ ሁሉንም ነገር እጥላለሁ። ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ ከአሁን በኋላ፡ በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ በሚገኙት ጥቅሶች ሁሉ፡ እከተልሃለሁ" ለምን አትሉትም? በክርስቲያናዊ ጥምቀት ካልተጠመቃችሁ፡ "እጠመቃለሁ፡ ጌታ ሆይ።"

178 "ገና መንፈስ ቅዱስን ካልተቀበላችሁ... " ስትቀበሉት ታውቃላችሁ። የሚያስፈልጋችሁን ዋሰትና እና ፍቅር እርሱ—ይሰጣችኋል። ኦህ፡ ልዩ ልዩ ነገሮች አርገህ ሊሆን ይችላል፡ ሰሜታዊ ሆነህ ይሆናል፡ ጮኸህ ወይም በልሳኖች ተናግረህ ሊሆን ይችላል፡ ያም ጥሩ ነው። ነገር ግን ያ መለኮታዊ

ፍቅር ከሌላችሁ፡ አሁን እመኑኝ፡ እንዲህ በሉት፡ “ጌታ ሆይ፡ በልቤ ውስጥ፡ በነፍሴም፡ የመንፈስህን ጉብኝት፡ መውደድ፡ ማክበር፡ እና ያ መለኮታዊ ፍቅር በልቤ ውስጥ እንዲኖረኝ፡ ዛሬ፡ እስከ መጨረሻው እስትንፋሴ ድረስ ወደዚያ ከፍታ እንዲወስደኝ ቅዱሱን መንፈስህን ሰጠኝ፡” እኛ እየጸለይን። እናንተም፡ አሁን፡ ጸልዩ። በራሳችሁ መንገድ፡ ጸልዩ፡ እግዚአብሔር እንዲያደርግላችሁ ጠይቁ።

179 እወዳችኋለሁ። እወዳችኋለሁ። እዚህ ጋር የተቀመጣችሁ፡ ጠንክራችሁ የሠራችሁትና ምስኪን ልጆችን የመግባችሁ ውድ ሽበታም-አባቶች! እናንተ፡ ከዓይኖቻችሁ እንባ ያፈሰሳችሁ ምስኪን አዛውንት እናቶች! እኅቴ ሆይ፡ ውዴ ሆይ፡ ይህን ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ፡ በሌላኛው እስትንፋስ ባሻገር ያለው እንደዚያ አይደለም። ይህ በእርግጠኝነት በዚህ ክፍል ውስጥ እንዳለ አምናለሁ። ልዩነቱ የምንኖርበት አድማስ ብቻ ነው። ይህ አሁን የምንኖርበት ጥፋት ብቻ ነው።

180 አብረን እየጸለይን፡ “ነገር ግን ፈቃድህ ይፈጸም ዘንድ፡ ጌታ ሆይ፡ ፍቃድህ በእኔ ትሁን።” ብላችሁ ጸልዩ።

181 ጌታ ሆይ፡ በአክብሮት፡ በቃልህ እና በቅዱስ መንፈስህ መሠረት፡ ከየት እንደተወልድን በማወቃችን በጣም ደስተኞች ነን። “ከሰው ፈቃድ፡ ወይም ከሥጋ ፈቃድ ሳይሆን፡ ከአምላክ ፍቃድ ስለተወለድን ደስተኞች ነን።”

182 ዛሬም፡ እንጸልያለን፡ አባት ሆይ፡ እነዚህ አሁን የምህረትን ጸጋ የሚጠይቁ፡ መንፈስህ ያንን ያድርግላቸው፡ ጌታ ሆይ። እኔ ይህን ማድረግ የምችልበት ምንም መንገድ የለም፥ እኔ ሰው ብቻ ነኝ፡ ሌላኛው የቂስ ልጅ ነኝ። ነገር ግን አንተን፡ ቅዱሱን መንፈስህን እንፈልጋለን።

183 እግዚአብሔር ሆይ፡ እንደ ሳሙኤል፡ የቃሉን እውነት የሚናገር እንድሆን ፍቀድልኝ። እስከ አሁንም፡ አረጋግጠህልኛል፡ ለአንተ ታማኝ እስከሆንኩ ድረስ፡ ወደፊትም ታረጋግጥልኛለህ ብዬ አምናለሁ።

184 አባት ሆይ፡ አሁን ሁሉም የዘላለም ሕይወት ያግኙ። ይህ ቀን ከእነሱ ፈጽሞ አይለይ። ይህን ዓለም ለቀው፡ በሚሄዱበት ሰዓት፡ አሁን የተናገርኳቸው ነገሮች፡ እውን እንዲሆኑ ይሁን። እኛም ሟች የሆንን፡ እዚህ ተቀምጠን፡ ዛሬ፡ ሰዓታችንን እያየን፡ እራታችንን እያሰብን፡ ስለ ነገ ሥራ ስለ ሕይወት ሃላፍፊነቶች እና ድካም እያሰብን፡ እዚህ ተቀምጠን አለን፡ ይህ ሁሉ በዚያ አይኖርም። ሁሉም ይጠፋሉ። ምንም ሃላፊነት አይኖርም፥ እና ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ ደስታ ብቻ ይሆናል። አባት ሆይ፡ ያንን ሕይወት፡ ለሁሉም ስጣቸው። እናም እባክህን...

185 አባት ሆይ፡ ምንም እንኳን እዚህ ከእኔ ጋር የማይስማሙ፡ ሰዎች ቢኖሩም፡ ሴቶችም ቢሆኑ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ የተገኘ ሰው ሁሉ ይህን ራእይ ስናገር የሰማኝ ሰው ሁሉ፥ እያንዳንዳቸውን፡ በዚያኛው ዓለም፡ እንዳገኛቸው እለምንሃለሁ። ነገር ግን፡ አባት ሆይ፡ ጠላት በእኛ መንገድ እንዲቆም ፈጽሞ አትፍቀድ። በዚያ እንድናገኛቸው፡ እና እነሱም እንዲሮጡ፡ እርስ በርሳችን ተያይዘን፡ እየጮህን፡ “ውድ ወንድማችን።” እየተባባልን፡ በዚያ እንደተገለጸው፡ ጌታ ሆይ፡ ለሁሉም፡ ለምወዳቸው ሁሉ፡ እና ለሚወዱኝ ሁሉ ይሁንላቸው። ጌታ ሆይ፡ እንዲህ እንዲሆን እጸልያለሁ። ሁሉንም እወዳቸዋለሁ። ይገኙበት፡ አባት ሆይ። አሁን

የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ። ይህን ለመቀበል፡ የበኩላቸውን ያድርጉ። በኢየሱስ ስም እጠይቃለሁና። አሜን።

186 ለታመሙ ሰዎች ለመጸለይ፡ ጥቂት ጊዜ ብቻ አለን። እዚህ ላይ ትንሽ፡ የታመመች ልጅ፡ እና ወንበር ላይ የተቀመጠች ሴት አያለሁ።

187 አሁን፡ ውድ ወንድሞቼና፡ እኅቶቼ፡ እባካችሁ በተሳሳተ መንገድ እንዳትረዱኝ። ምን—ምን እንደተከሰተ አላውቅም። ምን እንደተፈጠረ አላውቅም። ነገር ግን፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ሰሞት፡ ወደዚያ እንድመለስ ፍቀድልኝ። ወደዚያ ሰፍራ እንዲሄድ ፍቀድልኝ፡ የትም ትሁን፡ መኖር የምፈልገው በዚያ ነው። ወደ ሦስተኛው ሰማይ እንደተወሰደው እንደ ጳውሎስ ለመሆን እየሞከርኩ አይደለም። ያን እያልኩ አይደለም። እሱ ለሚመጣው አዲስ አገልግሎት እኔን ለማበረታታት እየሞከረ፡ እኔንም የሚገፋፋኝ ትንሽ ነገር ሊሰጠኝ፡ እየሞከረ እንደነበር እምናለሁ።

188 እዚህ ላይ አንድ ደቂቃ ብቻ፡ አንድ ነገር ባነብ ምን ይመስላችኋል? ችግር የለውም? በአገር አቀፍ ደረጃ በቀዳሚነት የሚታወቅ አንድ መጽሔት፡ ቢሊ ግራሃምን፡

> **ይህ አፍሪካን ታይምስ** በመባል የሚታወቅ መጽሔት፡ **ዶክተር ቢሊ ግራሃምን፡** የካቲት አስራ አምስት 1960 ዕትም ላይ፡ ከፊት ገጽ ጋበዘው። ጸሐፊ፡ ሙስሊም፡ ወይም የመሐመድ ተከታይ የሆነ ሰው፡ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው የሆነው የክርስቶስ ሰብከት፡ ተአምራቶች ሊከተሉት ያስፈልጋል ብሎ የሚያስብ ሰው ነው። ሰንናገር እንዲህ እንላለን፦ "እንደሚከተለው፤ ክርስቶስ ለተከታዮቹ፡ እንዲህ በማለት ቃል ገብቶላቿል፡ 'በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፥ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።' ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የ—የተገለጹትን፡ የክርስቶስን ባህርያትና፡ ሥራዎች ሰርታ ታውቃለችን? በዛሬው ጊዜስ ማድረግ ትችላለችን? "የሚበልጡ ሰራዎች" ይቅርና፡ ክርስቶስ የፈጸማቸውን ተአምራቶች ግማሹን ማድረግ ራሱ፡ መለየት የምትችል ቤተክርስትያን አለችን? እንደ አንድ ግለሰብ፡ ታዋቂ፡ የክርስትና ቃል አቀባይ፡ እንደመሆንህ መጠን፡ ሙታንን ከሞት በማስነሳት፡ ወደ ሕይወት መመለስ ትችላለህ? በባሕር ላይ መራመድ ትችላለህን? የታመሙትን መፈወስና ዕውሮች ማየት እንዲችሉ ማድረግ ትችላለህን? ከላይ በተጠቀሰው ዘመን መሠረት፡ የሙሐመዳውያን ወይም፡ የክርስቶስ ተከታዮች፡ በእምነታችሁ የአንዳንድ ሰዎች አባባል፡ እንደነበረ የተቀመጠው፡ ወይም፡ የተቀመጠው፡ ይህ አይደለም?'" የሙስሊሙ አገላለጽ ከአንድ ስህተት ወደ ሌላ ስህተት ነው።

189 ይህን ሙስሊም ይቃወሙታል፡ ግን እሱ ትክክል ነበር። ይሁንና እንዲህ ማለት ነበረባቸው፡

> መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና፡ ቁርዓንን ማወቅ፡ ከሁሉ የተሻለ መልስ ነው። ቍርኣን የሚታገሰው... በ... በንጽጽሩ የሚታገሥ ነው። "ሙሐመዳዊነት የላቀ እና ክርስትናን የሚበልጥ ነው" የሚለው እሳቤ፡ ግልጽ የሆነ፡ (ጉ-ራ) ጉራ ነው (ብዬ እገምታለሁ) ምናባዊ ነው።

ይሁን እንጂ፡ ጸሐፊው፡ የቤተ ክርስቲያንን ተአምራት በሚመለከት አንድ ወሳኝ ነጥብ አንስቷል። ነገር ግን አሁንም የጸሐፊውን ሐቀኝነት እንጠራጠራለን፡ ምክንያቱም ሬቨረንድ. ዊልያም ብራንሃም የተደረጉ ተአምራት ማን ይጠራጠራል ወይም ይከራከራቸዋል በደቡብ አፍሪካ ከሚገኙት ሙስሊሞች፡ አስር ሺህ ክርስቶስን እንደ አዳኝነት በተቀበሉበት ጊዜ በደርባን፡ በደቡብ አፍሪካ፡ እና በመላው ዓለም ጭምር፡ በዊልያም ብራንሃም አገልግሎት፡ ወይስ በምስራቅ አፍሪካ በ ቲ. ኤል. ኦስቦርን ማን ይጠራጠራል? እርግጥ ነው፡ መቶ በመቶ ለቢሊ ግራሃም እንቆምለታለን። በጥያቄው ጭብጥ ዙሪያ፡ ተነጋገርን... ይህ ጥያቄ ምንም ቁምነገር የለውም።

190 ነገር ግን በእያንዳንዱ ክፍል መሐል ላይ (እነሱ ስለ እኛ... የሚያደርጉትን የማያውቁ፡ አክራሪዎች ናቸው ብለውናል።)፡ ለማንኛውም፡ በጋዜጣቸው፡ እግዚአብሔር እንዳደረገው፡ መመስከር ነበረባቸው። እግዚአብሔር ዛሬም፡ እንደ ቀድሞው፡ ያው እግዚአብሔር ነው።

191 እነሱ አያዩትም፡ አያምኑም ብላችሁ አታስቡም ይሆናል። የተደበቀ ነገር አይደለም፥ በጥሻ ውስጥ የተደረገም አይደለም።

192 እና በመቶ ሺዎች የሚቈጠሩ ሰዎች እዚያ ተቀምጠው፡ አይተውታል። ያ አካል ጉዳተኛና፡ ስቃይ ውስጥ ያለ ልጅ ወደዚያ ሲመጣ፡ መንፈስ ቅዱስ ስለ ሕይወቱ፡ እና ስለ ነገሮች፡ እና እዚያ ውስጥ ስለተከናወኑ ነገሮች ሲነግረው አይተዋል። አሥር ሺህ ሙስሊሞች መሬት ላይ ሲወድቁ፡ ለጥ ብለው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ የግል አዳኝ ሲቀበሉ አይተዋል።

193 አሁንም እንደነ ቲ. ኤል. ኦስቦርን፡ እና የመሳሰሉት፡ አሁንም በጎችን የሚመግቡ አሉን። ወንድም ኦስቦርን ገና በሙስሊሞች መካከል የተረሳ አይመስለኝም። በጣም የበላይ የሆኑ ይመስላቸዋል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በጐችን ከአንበሳ፡ እና ከድብ የሚያድን አምላክ አለን።

194 ይህን መጻፋቸውን እና ማወቅ መቻላቸውን ማወቄ ጥሩ ሆኖልኛል። አይ፡ እንደማያውቁ ያስባሉ፡ ይሄዱና ጀርባቸውን ይመልሱና፡ እንዲህ ይላሉ፡ “እህ፡ እነዚያ ቀናትማ አልፈዋል።”

195 ሙስሊሙ እንዲህ በማለት ጠየቀ፡ “አልፈዋል እንዴ? እንደዚያ ከሆነማ መላው መጽሐፍ ቅዱስም አልፏል። ሁላችሁም ተሳስታችኋል። እናንተ ሰው እያመለካችሁ ነው፡ አንድን የሞተ ሰው እያመለካችሁ ነው። ሰሙ ኢየሱስ ነበር። ከብዙ ዓመታት በፊት፡ የሞተ ከመሆኑም በላይ፡ ከሞት ስለመነሳቱ የሚያሳይ ምንም ነገር የለም።”

196 በደርባን ስብሰባ ላይ ግን እንዲህ ሊሉ አልደፈሩም። በዚያማ በምድር ላይ እያለ ያደረገውን ሁሉ እያደረገ፡ አረጋገጠላቸው። አሁን የ——-የሃይማኖት ተቋማት እንኳን ወደ ኋላ መመለስ አለባቸው፡ መለስ ብዬ አስተምህሮዬን በመጽሐፍ ቅዱስን መፈተሽ-እንዳለብኝ የጻፈልኝ ያንን ሰው፡ በጋዜጣቸው ላይ ማስፈር የነበረበት እሱ ነበር። ከዚያ በኋላ፡ ያም ሆነ ይህ፡ ምንም ቢሆን፡ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ያደርጋቸዋል። ትክክል ነው። ያም ሆነ ይህ፡ እንዲያመሰግኑት ያደርጋቸዋል።

197 እዚህ ጋር፡ የታመመች ልጅ አያለሁ። ልጅሽ ናት? እህቴ፡ ችግሯ ምንድን ነው? [ያቺ እህት “የአንጎል ውስጥ ደም መፍሰስ ነው፡” አለች።—አርታዒ።] እምቤት? [“የአንጎል ውስጥ ደም መፍሰስ።”] የአንጎል ደም መፍሰስ። [“ከበርካታ ዓመታት በፊት፡ ሰለ እሷ የአንጎል ደም መፍሰስ፡ ጽፌላችኋለሁ።”] ኦህ፡ አዎን። [“የዛሬ አራት ዓመት፡ በነሐሴ ወር እንደታመመች ነው።”] በነሐሴ ወር፡ አራት ዓመት። [“ወንድም ኔቪል እሷን ለማየት ሄዶ ነበር።”] ኦህ፡ ከማሪንጎ ነው፡ ወይም በዚያ አቅራቢያ የሆነ ቦታ? [“ፓኦሊ።”] ፓኦሊ። ታዲያ፡ ልጅቷ ይህች ነች? እናት፡ ልጇን ሊያድናት የሚትችለው፡ አንድ ነገር ብቻ ነው፥ እሱም፡ እግዚአብሔር እሷን በማወቁ ብቻ ነው። [“ከዚያን ጊዜ አሁን በጣም ደህና ናት።”] በጣም ደስ ብሎኛል።

198 ወንድም ኔቪል፡ ልትጸልይላት ወርደህ ታውቃለህ? [ወንድም ኔቪል “አዎን፡ ጌታዬ፡” አለ።—አርታዒ።] ወንድም ኔቪል ወርዶ ከጸለየላት ጀምሮ፡ ተሽሏታል። አሁንም የበጐችን ምግብ የሚያውቁ እረኞች አሉን።

199 እዚያ በወንበሩ ላይ የተቀመጥሽ፡ ውድ እህታችን፡ የአንቺ፡ ችግር ምንድን ነው? [አንዲት እህትም “ካንሰር አለባት፡” አለች።—አርታዒ።] ካንሰር።

200 መልካም፡ ምናልባት እዚያ ጋር ሆነሽ፡ አንድ ነገር ልጠይቅሽ። እዚህ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች ከ... ከካንሰር ተፈውሰዋል? እጃችሁን አንሡ። ተመልከቺ፡ እኅት። [“መስማት የተሳናት ናት፡ የምትላትን መስማትም አትችልም።”—አርታዒ።]

201 እግዚአብሔር ፈዋሽ ነው። ይህን እናውቃለን። ወደዚያ ሄጄ የደም መፍሰሱን ከልጅቷ ላይ ማስወገድ እንደምችል ወይም፡ ደግሞ ካንሰርን፡ ከሴትየዋ ላይ ማስወገድ እንደምችል ብነግራችሁ፡ እሳሳታለሁ። አንድ ነገር ግን አውቃለሁ፡ አንድ ድብ ይመጣ ነበር (ካንሰር፡ እጢ፡ መታወር፡ ሞትም) የእግዚአብሔር በጎችን ይይዛቸው ነበር፡ አንድ ቀን ግን፡ እኔም በእግዚአብሔር ሃይል ጋር ወጥቼ፡ አርደውና የእግዚአብሔርን በግ ከእጁ እሰጥል ነበር። ያ ትክክል ነው። ዛሬም የምንወጣው፡ **እከሌ-እና-እከሌ**፡ በሚል በማንም ታላቅነት አይደለም። ከትንሽ ከጸሎት ወንጭፍ ጋር እወጣለው። እርሱም ያስጥላታል።

202 ያንን ታምኛለሽ፡ አይደል፡ እህት? አንቺም፡ ታምኛለሽ፡ አይደል፡ እህት? ሰንቶቻችሁ አሁን በልባችሁ ታምናላችሁ?

203 አሁን እኔ ሰጸልይ አንገታችሁን ዝቅ አድርጉ።

204 ውድ አባቴ ሆይ፡ አንተ ካልረዳሃት በስተቀር፡ መራመድም ሆነ መዞር የማትችል፡ አንዲት ቆንጆ ወጣት፡ እዚህ ተኝታለች። ጠላት ይዟታል። ከሐኪሞች አቅም በላይ ነች። ዶክተር ምንም ነገር ማድረግ እስኪያቅተው ድረስ፡ ጠላት በድንገት ወደ ብዙ ርቀት ወደ ጠፈር ወሰዷታል። ከአንተ አቅም በላይ ግን አይደለችም፡ ጌታ ሆይ። እጅህን በእሷ ላይ መጫን በምትችልበት ቦታ ላይ ነች። እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት፡ እጄን በዚህች ወጣት ሴት ላይ እጭናለሁ፡ ይህንም የአንጎል ደም መፍሰስ እገስጻለው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደገና፡ ወደ ቀድሞ ጠንነቷ እጠራታለው። ለእግዚአብሔር ክብር ትኖራለች። ልክ ሌሎች በሰላም፡ ወደዚህ ቤተክርስቲያን የመጡት፡ ገብተው እንደሚወጡ፡ እሷም ደህና ትሁን፡ እግዚአብሔርን አመሰግኑ። በኢየሱስ ክርስቶስም፡ ይሁን።

205 በጥቂት ጊዜ ውስጥ፡ ጸጉሩዋ እየሸበተ እንደሆነ ሁሉ፡ ወጣት እንጂ፡ የሸመገለ ወዳላየሁበት ከአድማስ ማዶ ወዳለው ምድር ልትሄድ ነው። የምትወዳቸው ሰዎች ግን፡ ስለሚወዷት፡ እያለቀሱ ይገኛሉ። እሷን የያዛት እና ዶክተር ሊደርስባት ከሚችለው በላይ ሩቅ የወሰዳት፡ ፈሪው የካንሰር አንበሳ ነው። እግዚያብሔር ሆይ፡ እኔ፡ ከእሷ በኋላ መጥቻለው። ነጥቄ ላወጣት መጥቻለሁ። እምባሳደር በሆንኩት፡ ተሸንፎ በማያውቀው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ያንን የካንሰር አምበሳ ቆራረጥኩት። ትቷት ይሂድ፡ ደህናም ትሁን፡ አሁንም፡ ለእግዚአብሔር ክብር፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ብዙ አመታትን ትኑር።

206 አሁን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ ያ ታላቅ ጋሻ፡ በተሞረደ ጦር፡ በጠቢብ ሰው ንግግር እና ቋንቋ አይደለም፡ ተራ በሆነው፡ በትንሽ የእምነት ወንጭፍ እንጂ። እኔ የመጣሁት ለዚህች ነፍስና፡ ለዚህ የካንሰር ጠላት ከዶክተሩ ተደራሽነት ባሻገር ስለወሰደው ሰውነት ነው። እኔ ግን ዛሬ ጠዋት፡ ለእሷ መጥቻለው፡ ጌታ ሆይ፡ እሷን ወደ ለመለመው መስክ እና ወደ እረፍት ውሃ ዘንድ ለመመለስ መጥቻለው። የእርሱ አምባሳደር በምሆን፡ በድል አድራጊው በኢየሱስ ስም። በእውነተኛ እምነት፡ ባደረግነው በጸሎታችን ኃይል፡ ተመልሳ ትመጣለች ብዬ አምናለሁ። ስለዚህ ይሁን... ? ...

207 (የጥምቀት አገልግሎት ያለ ይመስለኛል። አለ አይደል? ) [ወንድም ኔቪል "አዎን፡ ጌታዬ። የሚጠመቁ ሰዎች ያሏቸው ሁለት ሰባኪዎች አሉ፡" አለው።—ዓርታኢ።]

208 ራሶቻችሁን ለአንድ አፍታ ታነሳላችሁ? ፓስተሩ አሁን እንደነገረኝ...

209 እነዚህ ሰዎች በጣም፡ በጸና ታመዋል። ሁሉም ደኅና ይሆናሉ። ብቻ አ... አትጨነቁ ችግር የለውም። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መቼም ቢሆን አይወድቅም። እናሳድደዋለን።

210 የጥምቀት አገልግሎት አለ። መሄድ ያለባቸዉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ዛሬ ማታ በድጋሚ አገልግሎት እናደርጋለን።

211 ዛሬ ማታ እዚህ ሊመጣ የማይችል፡ አሁን እንድንጸልይለት የሚፈልግ ሰው አለ፡ ማታ ተመልሶ መምጣት የማይችል ሰው አለ? ዛሬ ማታ መምጣት የማትችሉ፡ አሁን ወደዚህ ኑ። ዛሬ ማታ፡ ከጸሎት መስመር፡ ተጨማሪ ጊዜ ይኖረኛል። እነዚህን ሰዎች ማጥመቅ አለባቸው።

212 እዚያ ጋር ህጻን ልጅ አለ? መልካም። [አንድ ወንድም አለ፡ "ይሄን ባቀብልህ መልካም ነው?"—አርታዒ።] አዎን፡ ወንድሜ። በጣም፡ አመሰግናለው። ትንሽ ቆይቼ ወይም አሁን ባነብ ችግር የለውም? አመሰግናለው፡ ወዳጄ።

213 አሁን አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ ብቻ ስጡኝ፡ ከዚያ በኋላ የ—የጥምቀት አገልግሎት እ—ናደርጋለን። ሁላችሁም እሱን ማየት እንደምትፈልጉ አውቃለው።

214 እና ዛሬ ጥዋት መጠመቅ የምትፈልጉ፡ መልካም፡ ሴቶች የሆናችሁ፡ እናንተ ልብሳችሁን ለመቀየር **በዚህ** በኩል እለፉ፡ ወንዶች ደግሞ **በዚህ** በኩል።

ከዚያም ለነዚህ ለታመሙ ሰዎች እየጸለይኩ ሳለው፡ እናንተ ለጥምቀት አገልግሎት ተዘጋጁ። እነዚያም አሁን...

215 አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ ትንሽ የ—የጸሎት መሰመር ለማድረግ እሞክራለው፡ ዛሬ ማታ፡ እንደመጡ ወድያው፡ እንደዛ አደርጋለው። እና ዛሬ ምሽትም፡ በኤፌሶን 1ኛ መጽሐፍ እንጀምራለን። የምትሄዱበት ቤተክርስቲያን ከሌላችሁ፡ እናንተን ለማስተናገድ በጣም ደስተኞች እንሆናለን። የራሳችሁ ፓስተር እና ቤተ ክርስቲያን ካላችሁ ግን፡ እንግዲህ—በምትደግፉት ውድ ቤተ ክርስቲያናችሁ ተገኙ።

216 መሄድ ካለባችሁና፡ በዚህ ጊዜ የምትሄዱ ከሆነ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ስትችሉ እንደገና ከእኛ ጋር ሁኑ። እናንተን በማግኘታችን ደስተኞች እንሆናለን።

217 እንዲጸለይልህ ፈልገህ ነው፡ ወንድም? ችግርህ ምንድን ነው? ከፍተኛ የደም ግፊት።

218 አሁን፡ መጸለይ ስለምንፈልግ፡ ሌሎቻችሁ፡ ለአንድ ደቂቃ፡ አንገቶቻችሁን ዝቅ አድርጉ።

219 አባት ሆይ፡ ዛሬ፡ ስለ ምስኪኑ እረኛው ወንጭፍ፡ አንበሳውን ስላንበረከከ ጸሎት፡ አመሰግንሃለሁ፡ ምስኪኑ በግ ከእርሱ ዘንድ ተናጥቆ፡ ወደ እናት አባቱ ተመልሷል። ለወንድማችን እፀልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ እርሱንም፡ በደህና እንድትመልሰው እጠይቃለሁ። የደም ግፊት እና የአካሉ ችግሮች ይቁሙ። ጌታ ሆይ፡ እሱን ለመመለስ፡ ከኋላው ወጣሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ይሁን። አሜን።

እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ።

ወደ ታች ስትወርድ፡ አይነ ሰውር ህጻን ልጅ፡ እንደያዝክ አይቻለሁ።

220 አንድ ተጨማሪ ነገር ማለት እፈልጋለሁ። እንዲህ ሆኜ... በጣም አሞኝ፡ ሲያስታውከኝ ነበር። እና እንዲህ ብዬ አሰብኩ... ከቻላችሁ፡ ይህ እንድያመልጣችሁ አልፈልግም። እንዲህ አሰብኩ፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ አንድ ሰው ከውጭ ይፈልግሃል ብባል ምን እሰጣለሁ? ምናልባት ሚስቴ 'ቢሊ፡ አንተን ለማየት አንድ ሸምገል ያለ ሰው መጥቷል፡' ልትለኝ ትችላለች።

221 "እነሆ ጥቂት ቆይቶ፡ ትንሽ መለጥ-ያለ በፊቱ ዙሪያ ግራጫ ጺም ያለው ሰው ይመጣል። ወደ ቤት ተራምዶ ይገባና፡ እንደዚህ ይላል፡ 'አንተ ወንድም ብራንሃም ነህ? '

''እኔም 'አዋን፡ ወዳጄ፡ እኔ ነኝ፡' እለዋለው።

222 "'ስሜ ስምዖን ነው።' እጁን በላዬ ላይ ጭኖ፡ ለአንድ ደቅቃ ያህል ያየኛል። 'አንተ አማኝ ነህ፡ ወንድም ብራንሃም፡' ይለኛል።

"'አዎን።'

223 '"ሁሉም ደህና ይሆናል።' የመጽሓፍ ቅዱሱ፡ ስምዖን ጴጥሮስ። አቤት እንዴት ደስ ባለኝ ነበር! ብዙ ነገር መናገር አይጠበቅበትም። እጁን ብቻ ጭኖብኝ፡ ደህና ሁን ማለት።"

224 ከዚያም በእግዚአብሔር እርዳታ፡ እና በእግዚአብሔር ቸርነት፡ በእኔ ላይ የመጣው ምንድነው፡ ወደ እነርሱ ብመጣ፡ በዚህ መልኩ የሚያምኑብኝ በአሰር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ። እኔም አሰብኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ እንግዲያውስ፡ ወደምችለው ሰው ሁሉ እንድደርስ አድርገኝ። ፍቀድልኝ—ብቻ... ”

225 እንዲህ አሰብኩ፡ “ሰምዖን፡ ወይም ጳውሎስ፡ አንዳቸው፡ ቢመጡ እና እንዲህ ቢሉኝ፡ ‘አንተ ወንድም ብራንሃም ነህ? ’

“‘አዎን።’

226 “እጃቸውን በእኔ ላይ ጭነው፡ ወደ እኔም እያዩ፡ እንዲህ ብቻ፡ ‘መልካም፡ ወንድም ብራንሃም፡’ ብለውኝ ቢሄዱ።

227 “እፈወሳለሁ። ደህና በሆንኩ ነበር። በእርግጠኝነት። እንዲህ አልኩ... አቤት፡ ወዲያው ድፍረት በተሰማኝ ነበር። ‘እፈወሳለሁ፡’ ባልኩ ነበር።” አዎን፡ ጌታዬ።

228 እና ዛሬም ተመሳሳይ ነገር የሚያምኑ ሰዎች አሉ። ወደ እናንተ የምመጣውም ለዛ ነው፡ እጄን በላያችሁ ጭኜ፡ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ።

229 እህቴ፡ ለአንድ ደቅቃ ያህል፡ ይህን ህጻን ልጅ ልያዘው። ዓይነ ሰውር፡ ህጻን ልጅ ነው። ለምን ያህል ጊዜ ዓይነ ሰውር ሆኖ ቆይቷል? [ያቺ እህት “ከተወለደ ጀምሮ፡” አለች።—አርታዒ።] ከተወለደ ጀምሮ።

230 ትንሹ ልጅ፡ እንዴት ነህ! ኦህ፡ አንተ በጣም ደህና ነህ፡ ትንሹ ልጅ... ? ...

231 ቸር አምላክ ሆይ! ይህ ትንሽ ልጅ ሲወለድ፡ ዓይነ ሰውር ሆኖ፡ ከሐኪሞች አቅም በላይ ሆኖ ተወልዷዋል፡ ይህ ቆንጆ፡ ፍቅር ይሆነ ምስኪን ልጅ፡ ማየትም አይችልም። ይህ ምስኪን ልጅ ገና በህወይት ለመኖር እድል ከማግኘቱ በፊት፡ ጠላት፡ ከዶክተሮች አቅም በላይ ነጥቆ ወስዶታል። ስለዚህ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከእሱ በኋላ እወጣለሁ፡ ጌታ ሆይ። በዚህ በቀላል፡ በትንሽ በጸሎት ወንጭፍ። ልመልሰው፡ ጌታ ሆይ። ጠላትን፡ ዲያቢሎስን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እገጥመዋለሁ፡ ይህን ልጅ ለእግዚአብሔር አሳልፌ እሰጣለው። ሰይጣን ከእሱ የዘረፈውን ነገር መልሼ ሰሰጠው፡ አይኑን ለእግዚአብሔር፡ አሳልፌ ሰጠሁ። አይን ይኑረው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይሆናል። አሁን፡ እንደዚያው ይሁን።

232 አሁን፡ ወድ፡ እህቴ፡ አሁን፡ ይህ ትንሽ ልጅ ደህና እንደሚሆን አንድም ጥርጣሬ እንዳይኖርሽ። እንዲህ እንድታደርጊ እፈልጋለሁ፡ ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን መልሰሽ አምጥተሽ፡ ማየት ችሏል ብለሽ፡ ለሰዎችም እንድታሳይ ነው፡ ያደርጊያለሽ፡ አይደል?

እይታውን ሰጠው፡ በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም... ? ...

233 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ብ... ብዙ ፀሎት ያደረግንላት ይህች ትንሽ ልጅ! ዛሬ ጠዋት፡ ግን፡ ይህን የሰጠኸኝን ትንሽ ወንጭፍ ይዤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንደገና እመጣለሁ። እናም ጌታ ሆይ፡ ከካንሰር አፍ... አወጣቸው ዘንድ፡ በገዛ ኃይልህ፡ በዚህ ረድተኸኛል፡ ሞተዋል ከተባሉበት ሞት እና ከቀዘቀዙ በኋላ፡ ከሞት አፍ ለማንሳት፡ በኃይልህ ረድተኸኛል። ከዚህ ከጠላት በኋላ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጥቻለሁ። ስለዚህ እንደገና ወደ ጥሩ ጤና መልሳት፡ ጌታ ሆይ። ይሁን። ለእግዚአብሔር ክብር፡ ይሁን።

234 አንቺም ይጸለይልሻል? [እንዲት እህት ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረች—እርታዒ።] አማኝ ነሽ? [“አዎን።”] ጌታ ሆይ፡ እሷንም ወደ ትንሿ ወንጭፍ ቦታ፡ አመጣታለው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ትቷት ይሂድ እንዳይመለስባትም።

235 [እንዲት እህት ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረች—እርታዒ።] መልካም፡ ያህ ተመሳሳይ ትንሽ ወንጭፍ፡ ሄዳ ወንድም ሃርሊን፡ ለሴት ልጅሽም እና ለራስሽ አገኘች።

236 አሁን፡ የሰማይ አባት ሆይ፡ የሰጠኸኝን ትንሽ ወንጭፍ ተጠቅሜ፡ ወደ ጠላትት መጣሁ፡ “ከልብህ ብትጸልይ፡ ህዝቡም እንዲያምንህ ብታደርግ፡” ብለኸኛልና፡ ትንሿ ድንጋይ ወደ መግደያ ቦታ ትድረስ። ጌታ ሆይ፡ ወደ ልመናዋ እወረውራለሁ፡ አሁን ይሂድ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንዲሁ ይሁን። አሜን።

237 [እንዲት እህት ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረች—እርታዒ።] እሺ፡ እህቴ። አሁን… ነርቭ ከዶክተሮች አቅም በላይ ነው። አንቺን ለማረጋጋት የሆነ ነገር ሊሰጡሽ ይችላሉ። ከዚያ በኋላ ግን፡ ያባብሰልሻል። አዎ። አሁን ተመልከቺ። ዛሬ ጠዋት፡ እናሳድደዋለን። አንቺን ተንጥቄ ለማምጣት፡ እሄዳለው። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ።]

238 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡… [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—እርታዒ።]… አምስት ትናንሽ ድንጋዮች፡ f-a-i-t-h፡ እና የጸሎት ወንጭፍ። እህቴን ከዚያ ነርቭ እጅ እየመለስኳት ነው… ? … ከርቀት። ወደ ሰላም እና ወደ ለመለመው መስክ እና ወደ እረፍት ውሃ ዘንድ እየመለስኳት ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህን አደርጋለው። አሜን።

[እንዲት እህት ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረች—እርታዒ።]

239 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ይህች ትንሽ ልጅ፡ ማስኩላር ዳይስትሮፊ ባለመሆኑ በጣም ደስ ብሎናል። ምንም ይሁን ምን ግን፡ አሁንም አንተ ትደርስበታለህ፡ ጌታ ሆይ። እኔም ከትንሽ ከእምነት ወንጭፍ፡ እና ከዚህ ድንጋይ ጋር መጣሁ። እናም ይህን ድንጋይ መጣል በሚችለው ጥንካሬ ሁሉ እወረውራለው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ዋናውን ቦታ ይምታ። እህታችን ደህና ትሁን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህን አደርጋለው።

[እንዲት እህት ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረችች—እርታዒ።]

240 እንደ እኚህ ወጣት እናት፡ እና ትንሹ ልጇ፡ በዚያ በእድማስ ማዶ ልታገኘው የምትወደው፡ በሌላ አድማስ፡ ቀደም ሲል በነገርኳችሁ በተከበረ ምድር ልታገኘው የምትፈልገው ትንሽ ልጅ፡ እነርሱም… እናትየዋ ት… ትንሹን ልጇን ለማሳደግ ትፈልጋለች፡ እናም አንተ ካልረዳሃው ትንሹ ልጅ ረጅም ጊዜ መቆየት አይችልም። እኔ ግን ወንጭፉ ይዤ መጣሁ፡ በጥንካሬ እና በጠላት ላይ ባነጣጠርኩት ኢላማ መጣሁ። ይህንንም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ በሱ ላይ ወነጨፍኩት። ለእግዚአብሔር ክብር፡ ደህና ይሆናል። በኢየሱስ ስም። አሜን።

[እንዲት እህት ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረች—እርታዒ።]

241 ኦህ፡ ያ በጣም ጥሩ ነው። ደስ ብሎኛል። መልካም፡ ያ አገልግሎት፡ የሰዎችን ትኩረት የምስብ ትልቅ አገልግሎት፡ ነበር። ወደ ሰራዎች ይጠቁማል… ? …

242 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ሰይጣን እቺን ምስኪን እናት ሀኪሞች ወደ ማይደርሱበት ቦታ ነጥቋታል። የሚችሉት መድኃኒት መወንጨፍ ብቻ ነው፡ ጌታ ሆይ፡ ያ እማ እሷን መጉዳት፡ ብቻ ነው። በብዙ ችግር ራሷን እንድትስት ያደርጋታል። ከዚያ ስትነቃ፡ ይብሰባታል። እኔ ግን ከዚህ ከእምነት ወንጭፍ ጋር፡ ከአንድ ድንጋይ ጋር፡ በቀጥታ ዒላማ በማድረግ፡ ወደ ኢላማው በመምራት መጣሁ። ለእግዚአብሔር ክብር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይህንን ጭንቀት ከእርሷ እወስዳለው። አሜን።

[የሆነ ሰው ከወንድም ብራንሃም ጋር ተነጋገረ—አርታዒ።]

243 አምላክ ሆይ፡ በቅርብ ጊዜ፡ ወንድም ጆርጅ እዚያው ተኝቶ፡ ሲሞት፡ እምነት ምን እንዳደረገለት አይቻለሁ። አሁንም ሪዮማቲዝም አሞታል፡ ጌታ ሆይ። ሕመሙን የሚያስታግስለት፡ አንዳንድ ኮርቲዞን መስጠት እንደሚችሉ ተገንዝበናል፡ ህመሙን ከላዩ ይወስዳል ማለት ግን አይደለም። ስለዚህ እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይህን ጸሎት አልመን እንጸልያለን። ሪዮማቲዝም ለቆት ይሂድ። ወደ ቤቱ ይሂድ ደህናም ይሁን።

አመሰግናለው፡ ወንድሜ።

244 እንዴት ነሽ፡ ዲሬ? [አንድ እኅት ከወንድም ብራንህም ጋር ተነጋገረች—አርታዒ።] ኦህ፡ ማይ! መስማት አለመቻል። ፈጽመሽ አትሰሚም? ኡህ-ሁህ። ብቻ ከመረዳታችን በላይ ነው! በጌታ በኢየሱስ ታምኛለሽ? ["አሜን።"] ከእነዚህ ቀናት መካከል በአንዱ፡ በዚያ ውብ ሴት ትሆኛለሽ። ለዘላለም ወጣት ትሆኛለሽ። አሁን ስለ ክብሩ መኖር እንደምትፈልጊ አውቃለሁ። ወደቀድሞ ለመመለስ...

245 [አንዲት እህት "አይ፡ ስለልጄ እያዘንኩ ነው፡" አለች።—አርታዒ።] ልጅሽ። ["ከሁለት ዓመት በላይ ጠፍቷል።"] እሱን ማግኘት አልቻልሽም? ["በእግዚአብሔር እጅ ነው።"] ኦህ፡ እርሱ—ሄዷል? ["ኡህ-ሁህ። በሞት ሸለቆ።"] ኦህ፡ ያ። ["የእኔም ሃዘን።"] አዎን። በኀዘን-ተውጠሻል። ["በኃዘን... በኃዘን-ተውጬአለሁ። እንዲህ ይሰማኛል፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ፡ እኔንም እንድወስደኝ እፈልጋለው። በእርሱ ካለኝ ደስታ በቀር ሌላ የለኝም።"]

246 እኅት ዲር፡ ጥሩ ስሜት ወደምሰማሽ ቦታ እንድትደርሺ እፈልጋለው። የዛሬ ጠዋት ራእዩን፡ ሰምታለች? [ሌላ እህት "እሷ በደንብ መስማት ትችላለች፡" አለች።—አርታዒ።] መልካም፡ አንቺ ንገሪያት።

247 መልካም፡ ምን እንደተፈጠረ እሷ ትነግርሻለች። ብቻ ከእስትንፋስሽ በላይ፡ ውድ ልጅሽ እየጠበቀሽ ነው። አንችም እንዴ እንደሱ ወጣት ትሆኛለሽ። ፍቅር፡ ፍቅር ብቻ... [ያቺ እህት "መቆየት አልፈልግም። የእግዚአብሔር ፍቃድ ከሆነ፡ ወደ እርሰ መሄድ እፈልጋለው፡" አለች።—አርታዒ።]

248 ውድ የሰማይ አባት ሆይ፡ የሕይወት ሩጫ ተጠናቋል። ብዙም የቀረ ነገር የለም። ከወንዙ ማዶ፡ የሚኖረው ውድ ልጇም፡ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ቢመለከት፡ "ጥቂት ቀናት ብቻ ነው፡" ይል ነበር። እሷም በደመናው በኩል፡ ወደ ክብር ምድር የምወስዳትን፡ ጀልባ በመጠባበቅ ላይ ነች፡ ጌታ ሆይ። አባት ሆይ፡ እባክህ ባርካት፡ ልቧንም አጽናናት። ከወንዙ ማዶ፡ ታላቅ ህብረት ይሁን።

60-0515M የተጠላው ንጉሥ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org